# ታማኝ ባለአደራ

(ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀ)

**(የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤ/ክ)**

**ዳላስ**

**ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት**

Ethiopian Evangelical Baptist Church

2822 S Jupiter Rd, Garland TX 75041

**www.wongelkedallas.org**
**www.eebc-dallas.org**
**Tel.2147030100**
**Fax 2147030161**

June 2012

# ታማኝ ባለአደራ ጥናት

## መግቢያ

ፍጹምና ቅን እንደነበረ የተመሰከረለት ኢዮብ የነበረውን ሁሉ ባጣ ጊዜ "ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፣ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔርም ነሣ፣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን" ሲል የነበረው ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንደነበረ መስክሯል (ኢዮ 1:21-22)። መጽሐፍ ቅዱስን ያስደገፈ ክርስቲያናዊ ባለ አደራነትን ስናጠና ኢዮብ በዚህ ክፍል የተናገረው እውነት ትልቅ መንደርደሪያ ነጥብ ነው። ይህ ክፍል የሚያስተምረን ነጥቦች አሉ።

1) ሰው "የእኔ ነው!" ሊል የሚችለው የራሱ የሆነ ነገር የለውም!

ኢዮብ እንዳመለከተው ሰው ወደዚህ ምድር ሲመጣ ራቁቱን ከመወለዱ ሌላ ይዞት የመጣው የራሱ ነገር የለውም (1ኛ ጢሞ 6:7)። ራቁቱን ከተወለደ በኃላ፤ እስትንፋስ እና አካሉን ያለ ሰው እግዚአብሔር በራሱ ሊጠብቃቸው የማይችል ፍጡር ነው።

2) ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው!

ኢዮብ ከላይ ባየነው ክፍል ያመለከተው ራቁቱን መወለዱን ብቻ ሳይሆን፣ የነበረው ሁሉ ከእግዚአብሔር ብቻ የተሰጠ መሆኑን ሲያስረዳ "እግዚአብሔር ሰጠ" ብሏል። ከዕለታት አንድ ቀን ራቁቱን ወደዚህ ምድር የመጣ ሕፃን፣ አድጎ ዕውቀት እና ሃብት እንዲሁም ወዳጆች ሲያፈራ ሁሉን በጥረቱ እና በጉብዝናው ያገኘው ይመስለው ይሆናል። እውነቱ ግን ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠው መሆኑ ነው። ቆም ብለን ብናስብ ከእግዚአብሔር ያልተቀበልነው፣ በራሳችን ያገኘነው ምን አለ? ለዚህ የምንሰጠው ምላሽ "አንዳች" የሚል እንድሚሆን እንገምታለን። ስለዚህ ባለ አደራዎች ነን ማለት ነው።

3) እግዚአብሔር ሁሉን የሰጠን ከአደራ ጋር ነው!

ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንደሆነ ያስተዋለው ኢዮብ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን በአግባብ ይጠቀም እንደነበረ ከኢዮብ መጽሐፍ ማስተዋል እንችላለን። ልጆቹን እግዚአብሔርን መፍራት ከማስተማር ሌላ፣ ስለ ልጆቹ ካለው ሃብት መስዋዕትን ያቀርብ ነበር።

ሚስቱ እግዚአብሔርን እንዲሰድብ በመከረችው ጊዜ እና ወዳጆቹ በፈረዱበት ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠውን አንደበት የማይገባ ነገር ተናግሮ እንዳይረክስበት ይጠነቀቅ ነበር። መላ ሕይወቱ በፈሪሃ እግዚአብሔር የተሞላ ስለነበር፤ "ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፣ ከክፋትም የራቀ ነበረ" ተብሎ ተመስክሮለታል(ኢዮ 1:1)። ኢዮብ እግዚአብሔር የሰጠውን ነገር የያዘበት መንገድ አንድ ቀን ሊያስጠይቀው ወይ ሊያሸልመው እንደሚችል በመረዳት ነበር።

አለን የምንለው ነገር ሁሉ ሰውነታችንን፣ ጤናችንን እና እስትንፋሳችንን ሳይቀር ከእግዚአብሔር የተሰጠን እንጂ በራሳችን ጥረት ያገኘነው እንዳይደለ ልንገነዘብ ይገባል። ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንደሆነ ካወቅን፣ ያለንን ሁሉ በአግባብ እና እግዚአብሔርን በመፍራት መያዝ እና ማስተዳደር እንዳለብን እናስተውላለን። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን ሰውነት፣ የግል ሕይወት፣ ቤተሰብ እና ወዳጆች፣ ያገኘነውን ገንዘብ እና ሃብት፣ እውቀት ፣ አገልግሎት … ሁሉንም በመጀመሪያ የእግዚአብሔር እንደሆኑ አውቀን የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ በአግባብ እንድናስተዳድር ይጠበቅብናል።

ስለ ባለአደራነት የተዘጋጀው ይህ ጥናት ይህንን እውነት ለማስተማር እና ለማስጨበጥ የተዘጋጀ ነው። እንግዲህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪዎች እና ተሳታፊዎች ሁሉ፣ በእያንዳንዱ ጥናት የተዘጋጁትን ንባቦች በሚገባ አንብበን ለጥናት ራሳችንን እንድንዘጋጅ ይሁን! እግዚአብሔርም በዚህ ጥናት የተሳታፊዎችን ልብ እንዲነካ እና ሁላችንንም እንዲያሳድግ፣ የትምህርት ዝግጅት ክፍል እና የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ነው።

የትምህርት ዝግጅት ክፍል

# ጥናት አንድ

**የአስተምህሮተ ባለአደራነት ትርጉም**

***ዓላማ፡-***

የባለአደራነትን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም በማስጨበጥ የጥናቱ ተሳታፊዎች እግዚአብሔር በአደራነት በሰጠን ነገሮች ሁሉ ላይ በታማኝነት አደራችንን መወጣት እንዳለብን ማሳሰብ።

***መግቢያ፡ -***

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ በተለይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ አደራ፣ ባለአደራ፣ መጋቢነት፣ አስተዳዳሪነት የሚሉ ግን ተመሳሳይ አሳብ ያላቸውን ቃላት ማግኘት እምብዛም የሚገርም አይደለም። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የባለአደራነትን ትክክለኛ ትርጉም መረዳት ግን ለብዙዎች አስቸጋሪ ነው። እንዲያውም የባለአደራነት ትምህርት ሲባል ብዙዎች የሚያስቡት ስለ ክርስቲያናዊ ገንዘብ አያያዝ እንዲሁም ለጌታ ቤት የሚገባውን አስራት እና መባ ስለመስጠት የሚያስተምር ትምህርት እንደሆነ ያስባሉ። በእርግጥም ይህ የአስተምህሮው አንደኛው አካል ቢሆንም ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባለአደራነት የሚያስተምረው ይህንን ብቻ አይደለም። ዛሬ በምንጀምረው ጥናታችን የባለአደራነት ትምህርት ብዙ አሳቦችን የምንዳስስ ሲሆን ለዛሬ ግን የባለአደራነትን ትርጉም እንመለከታለን።

ከጥሬ ቃሉ እንኳ ብንነሳ ባለአደራ የሚለው ቃል ሁለት አብይ ነጥቦችን ማለትም አደራ ሰጪ እና አደራ ተቀባይ መኖራቸውን ያሳስበናል። አደራ ሰጪው የአደራው ባለቤት ሲሆን አደራ ተቀባዩ ግን አደራውን በታማኝነት እንዲወጣ ወይንም እንዲያስተዳድር ሃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው። የአንድ ጉዳይ ወይንም ንብረት ባለቤት ጉዳዩን ወይንም ንብረቱን ለሌላው ወዳጁ በአደራ ሃላፊነትን የሚሰጠው ለታማኝ ሰው እንደመሆኑ ሁሉ፣ አደራ ተቀባዩም እንዲሁ፣ ታማኝነቱን ላለማጉደል፣ በጥንቃቄ እና በታማኝነት የተሰጠውን ሃላፊነት ይወጣል። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የባለአደራነት ትምህርት በዚህ አሳብ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፣ የትምህርቱ ፍሬ አሳብ የሚነገረን እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ባለቤት መሆኑን እና እኛ ሰዎች ግን በእኛ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔር ነገር ሁሉ በታማኝነት እንድናስተዳድር አደራ የተሰጠን ሰዎች መሆናችንን ያስገነዝባል። ይህንን አሳብ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥቂት አሳቦች መረዳት እንችላለን።

1) **እግዚአብሔር የሁሉ ባለቤት ነው።**

ሀ. **እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው።**

መጽሐፍ ቅዱስ ሲጀምር “በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድርን ፈጠረ” በማለት የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደሆነ ያሳስበናል (ዘፍ 1:1) ። ይህ የሚያሳስበን ባጭሩ በአለማት መካከል እግዚአብሔር ያልፈጠረው ወይንም በራሱ የተገኘ አንዳችም ነገር አለመኖሩን ነው። ይህ እውነት በዘፍጥረት ውስጥ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ አስረግጦ የሚናገረው እውነት ነው (ዮሐ 1:3፣ ሐዋ 17:24፤ 14:15)።

ለ. **ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ንብረት ነው።**

እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንደመሆኑ፣ በሰማይም ሆነ በምድር ያለው ሕያው እና ግዑዝ የሆነው ሁሉ ንብረትነቱ የእግዚአብሔር ነው። ዳዊት በመዝሙሩ “ምድር እና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፣ ዓለምም በእርስዋ የሚኖሩ ሁሉ” ሲል ይህንን እውነት አስጨብጧል መዝ 24:1።

እንግዲህ ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ነው ሲባል ሁሉም ነገር ነው። በሌላ አባባል፣ እኛም ራሳችን የእግዚአብሔር ንብረቶች ነን። ነፍስ እና ሕይወታችን፣ ያለን ንብረት፣ እውቀት … አለን አተረፍን የምንለው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው።

- ሰው ያለው የሰውነት አካል የእግዚአብሔር ነው፤ ሰውን በመጀመሪያ ከምድር አፈር ያበጀው ኋላም የሚመጡት ትውልዶች ከአንዱ አዳም እንዲወጡ ያደረገው እግዚአብሔር ነውና (ዘፍ 2:7፣ ሐዋ 17:26-27)።

-	ሰው ያለው የሕይወት እስትንፋስ/ ነፍስ የእግዚአብሔር ነው፤ ለሰው የሕይወትን እስትንፋስ የሰጠ እግዚአብሔር ነውና (ዘፍ 2:7)።

-	ሰው አለኝ አተረፍኩ የሚለው ንብረት፣ እውቀት እና ችሎታ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፤ “ብርና ወርቁ” ሁሉ የእግዚአብሔር ስለሆነ (ሐጌ 2:8) ደግሞም ከእግዚአብሔር ካልተቀበለ በስተቀር የሚያገኝ ስለ ሌለ (1ኛ ቆሮ 4:7)።

ባጭሩ እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ እኛንም ጨምሮ የሁሉ ነገር ፈጣሪ እና ባለቤት ነው (ራዕ 4:11)።

2) ሰው ያለው እና የሆነው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር በአደራነት የተቀበለው ነው።

ሰዎች ያለቸውን የገንዘብ ብዛት፣ የእውቀት ምጥቀት እና የችሎታ ርቀት ቆጥረው፣ በጉብዝናዌ ወይንም በጥበቤ ብዛት ያገኘሁት ብለው ብዙ ጊዜ ይመካሉ። ሆኖም ግን ከላይ እንዳየነው እና መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ እንደሚያስተምረን ሰው በራሱ ያገኘው ነገር የለም - ስለዚህም የሚመካ ቢኖር መመካት ያለበት ሁሉን በሰጠው በእግዚአብሔር ነው (ኤር 9:23-24)።

በመጀመሪያ ከላይ እንዳየነው ሰውን የፈጠረው እና እስትንፋስን የሰጠው እግዚአብሔር ነው (መዝ 100:3 ፤ 104:29፤ ሐዋ 17:25)። በሁለተኛ ደረጃ ግን ሰው በሕጻንነት ከእናት ማህጸን ሲወጣ ወደዚህ ምድር የሚያመጣው የራሱ ነገር የለውም (1ኛ ጢሞ 6:7)። ነገር ግን ሕጻን ከተወለደ በኋላ እግዚአብሔር በሚሰጠው ጸጋ እና ስጦታ ያድጋል፣ አገኘሁት ደረስኩበት የሚለውን ሁሉ ይቀበላል። ሰው ከእግዚአብሔር ያልተቀበለው ነገር የለም።

ሰው ሁሉን በአደራነት የመቀበሉ ማስረጃ ግን አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት መጠየቁ ነው። ጉዳዩ ጌታ በማቴ 24:45-51 የሰጠውን ምሳሌ የሚመስል አይነት ነገር ነው። አንድ ጌታ ወደ ሩቅ አገር ሲሄድ ታማኝ አድርጎ ለቆጠረው ባሪያ ቤተሰቡን በሚገባ እንዲያስተዳድር አደራ ሰጥቶት ይሄዳል። ያ ባሪያ ጌታውን እና አደራውን አክብሮ በታማኝነት ቢሰራ እና ጌታው በድንገት ቢመጣ፣ ታማኝነቱን ጠብቋልና ለሌላም ይሾማል፣ ነገር ግን ባሪያው ቢከፋ እና እንደማይገባ ሲመላለስ ጌታው ቢመጣበት፣ ስለጥፋቱ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ተገቢውን ቅጣት ይሰጠዋል። ጌታ እኛን ባለ አደራ አድርጎ ሲሾመን ልክ እንደዚሁ ነው። በአደራነት የሰጠንን ነገር በሙሉ እንዴት እንደያዝነው ሊጠይቅ ጌታ ይመጣል፤ ስለሰራነው ነገር በሙሉ በጌታ ፍርድ ወንበር ፊት ቀርበን መልስ እንሰጣለን (2ቆሮ 5:10 )።

# መደምደሚያ

ከላይ እንዳየነው የባለ አደራነት ትምህርት በኛ እጅ ያለውም ሆነ የሌለው ሁሉ የእግዚአብሔር እንደመሆኑ በኛ ስር ያለውን በአደራ ማስተዳደር እንዳለብን የሚያስተምር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው። ይህ አሳብ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባለ አደራ፣ መጋቢነት፣ አስተዳዳሪ፣ ገዢ፣ መሪ ተብሎ የተተረጎመ ሲሆን አሳቡ ግን እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ባለቤት መሆኑን እኛ ሰዎች ደግሞ የእግዚአብሔር አደራ ተረካቢዎች እና አስተዳዳሪዎች መሆናችንን የሚያስገነዝብ እውነት ነው።

የውይይት ጥያቄዎች

1.በአደራ ሰጪ እና ፣ በአደራ ተቀባይ መካከል ያለው ዝምድና እና ልዩነት ምንድን ነው? አደራስ ምን ማለት ነው?

2. የአደራው ባለቤት ለተቀባዩ አደራ እንዲሰጠው የሚያደርገው በአደራ ተቀባዩ ውስጥ የሚኖር ምን አይነት ባህርይ ነው?

3.በማቴ 24፡ 45-51 ባለው ክፍል ጌታ በሰጠው ምሳሌ መሰረት፣ ከባለ አደራ ስለሚጠበቅበት ባህርይ ምን ይነግረናል?

4.እኛ ለፍተን እና ጥረን የምናገኘውን እውቀት፣ ችሎታ እና ጥሪት የኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው የምንለው ለምንድን ነው?

6.ሰው በሆነው እና ባተረፈው ነገር ሁሉ መመካት የማይገባው ለምንድን ነው?

7.የሰውንም ሆነ የእግዚአብሔርን አደራ በታማኝነት እና በሚገባ አለመወጣት የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?

# ጥናት ሁለት

**ባለአደራነት በተሰጠን ገንዘብ እና ሃብት ላይ**

***ዓላማ፡-***

ዛሬ በእጃችን ያለው ጥሬ ገንዘብም ሆነ ንብረት ከእግዚአብሔር ዘንድ በአደራነት በአግባብ እንድናስተዳድረው የተሰጠን መሆኑን በመረዳት እንደ እግዚአብሔር ቃል እንድንጠቀምበት ማሳሰብ ነው።

*መግቢያ፡-*

አያያዙን ላላወቀበት፣ ገንዘብ አደገኛ ነገር ነው! አደገኛም ከመሆኑ በላይ፣ ጌታም በተራራው ስብከት ጊዜ እንዳስተማረው፣ ሰው በአንድ ጊዜ ገንዘብንም ወዶ ጌታንም ወዶ መኖር አይችልም። ገንዘብ የአምላክን ቦታ የሚሻማ፣ ለሚወዱት ደግሞ እግዚአብሔርን ከመከተል የሚያስጥል ወጥመድ ነው (ማቴ 6:24) ። ለዚህ የአስቆሮቱ ይሁዳን ሕይወት ልብ ብሎ ማየት ጥሩ ማስረጃ ይሆናል።

በሌላ በኩል ገንዘብ እና ንብረት ሰው ከእግዚአብሔር የሚቀበለው ስጦታ ነው። ገንዘብ አደጋ የሚሆነው፣ በራሱ ክፉ ስለሆነ ሳይሆን፣ ሰው ለገንዘብ ፍቅር ሲኖረው ወይንም ስለገንዘብ ያለው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን ሲቀር ነው ። ሰው ለገንዘብ ያለው አስተሳሰብ እና ፍቅር መስመር ሲለቅ፣ የክፋት ሁሉ ስር ይሆናል (1ኛ ጢሞ 6:19)። ስለዚህም በዛሬው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ ለገንዘብ እና ለሃብት ሊኖረን ስለሚገባው አመለካከት እና አጠቃቀም የሚያስተምረንን እንመለከታለን።

1) ***ገንዘብ ለሰው ልጅ እርካታ አያመጣም***

ሰዎች ብዙ ገንዘብ ቢኖራቸው ሁሌም ደስተኛ እንደሚሆኑ ያስባሉ። ስለዚህም ብዙ ብር እና ሃብት ለማካበት ከሚገባው በላይ ሲደክሙ እና ዋጋ ሊሰጡት የሚገባውን ብዙ ነገር ገንዘብ ስለማግኘት ሲሉ ሲጥሉ ይታያሉ። ሆኖም ግን እንደ እውነቱ ከሆነ ገንዘብ እና ጥሪት ለሰው ደስታ እና እርካታ አይሰጡም።

በመጀመሪያ ገንዘብ ያካበተው ከደሃው እኩል አንድ ቀን ይሞታል (መዝ 49:12 አዲሱ መደበኛ ትርጉም)። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ገንዘብን ለሚወድ ባለው ገንዘብ እንዲረካ ከመርዳት ይልቅ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብን የማግኘት ጥማትን፣ ባለው አለመርካትን የሚያመጣ ነገር ነው (መክ 5:10-12)። በገንዘብ ብዛት ለዘለቄታው እረካለሁ፣ እደሰታለሁ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው።

የገንዘብ ፍቅር እርካታ ካለማምጣቱ ሌላ ወዳጁን አደጋ ላይ የሚጥል ወጥመድ ነው። በገንዘብ ፍቅር ልቡ የተነደፈ ሰው፣ ገንዘብን ለማግኘት ከመስረቅ እና ራስን ለነውር ከመሸጥ አንስቶ ሰውን እስከመግደል አልፎም ጌታን እስከመሸጥ የሚያደርስ የክፋት ሁሉ ስር ነው። ሰው ባዳነው ጌታ ልቡ ካልረካ በገንዘብ ብዛት አይረካም።

**2) ገንዘብን በአግባባ አለመጠቀም**

መጽሐፍ ቅዱስ የገንዘብን አደገኝነት ቢያስተምርም፣ አንድም ቦታ ገንዘብ አላስፈላጊ እንዳልሆነ ወይንም ሰው ሊደርስበት የማይገባ እንደሆነ አድርጎ አያስተምርም። ገንዘብ እንደ እሳት ነው። እሳትን በአግባቡ ከያዙት እንደሚጠቅም፣ አላግባብ ከያዙት ደግሞ እንደሚያቃጥል ብሎም አገር እንደሚያጠፋ ገንዘብም እንዲሁ ነው። ገንዘብ አላግባብ የሚያዝበት መንገድ ብዙ ቢሆንም ጥቂቱን መዘርዘር እንችላለን።

*ሀ.* ***ገንዘብን የማጠራቀም ብቻ አደጋ***

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን ለነገ የሚጠቅመውን ማስቀመጥ እንዳለበት በሚገባ ያስተምራል። እንኳን ሰው፣ ገብረ ጉንዳን እንኳ ለነገ የሚጠቅማትን ታከማቻለች (ምሳ 6:6-11)። ሆኖም ግን ሰው፣ በአጠገቡ ያለውን ችግረኛ ዞር ብሎ ለማየት እስከሚያቅተው፣ ለጌታ ቤት የሚገባውን ማምጣት እስኪሳነው፣ ልፋቱ እና ጥረቱ ማጠራቀም ብቻ ሲሆን አደጋ ነው። ሰው ያጠራቀመውን ሁሉ ጥሎ ወደ ጌታ እንደሚጠቃለል ማስተዋል አስፈላጊ ነው (መክ 2:18-23፣ ሉቃ 12:13-21)።

*ለ.* ***ገንዘብን ሳያጠራቅሙ የማውጣት ብቻ አደጋ***

ከላይ እንዳየነው፣ እግዚአብሔር የገብረ ጉንዳን አሰራር ተመልክተን ለራሳችን ልብ እንድንገዛ ይመክራል (ምሳሌ 6:6-11) ። ሰው የሚያገኘውን ሁሉ በአንድም በሌላም መልኩ የሚያስቀምጠው እስከማይኖር ድረስ

ያለውን ሁሉ የሚያወጣ ከሆነ ያ ሌላው አደጋ ነው። ነገ ችግር የመጣ ዕለት፣ ለራሱም ከመቸገር አልፎ የሰው እጅ ጠባቂ ይሆናል።

ሐ. **የመበደር ችግር**

በመሰረቱ ሰውን ለብድር የሚያስገድደው አንደኛው በአግባብ አለማጠራቀም/አለመጠቀም ሲሆን ሌላኛው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው። ከአቅም በላይ የሆነ ችግር በመጣ ጊዜ መበደር አስተዋይነት ቢሆንም ከገንዘብ አያያዝ ጉድለት እና ከልቅነት የሚመጣ ብድር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የማይደገፍ ነገር ነው። ዛሬ ባለንበት ዘመን ብድር ስሙን አሳምሮ በክሬዲት ካርድ ስም ብዙ ሰዎችን አደጋ ላይ እየጣለ ያለ ነገር ነው። እንደዚህ አይነቱ ብድር ተገቢ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል። ገቢውን በአግባብ ካለመያዝ እና ያለኝ ይበቃኛል ማለት ካለመቻል የተነሳ የሚመጣ ብድር ሁሉ የባለአደራነትን ሃላፊነት መጣል ነው። ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ በአንድ በኩል ከፍቅር በስተቀር በማንም ላይ ዕዳ እንዳይኖርብን ሲያሳስብ፣ (ሮሜ 13፡8) በሌላ በኩል ደሞዛችን እንዲበቃን እና ኑሮዬ ይበቃኛል ማለትን እንድንማርም ያዛል (ዕብ 13:5፣ ሉቃ 3:14)።

3. ***መጽሐፍ ቅዱሳዊ የገንዘብ አጠቃቀም***

ከላይ እንዳየነው፣ ክርስቲያን ከሚያገኘው እንዲያስቀምጥ የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። ሆኖም ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል አከማቸ / አስቀመጠ የሚባለው ከጌታ ጋር ሲያከማች ነው። ከጌታ ጋር የማያከማች፣ በሉቃ 12:13-21 እንደተጠቀሰው ባለጠጋ ይበትናል። ከጌታ ጋር ማከማቸት ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ከጌታ ጋር ማከማቸት እንደ እግዚአብሔር ቃል ለጌታ የሚገባውን ለጌታ እየሰጡ፣ ሊረዳ የሚገባውን ሰው እያሰቡ፣ ለነገ ማስቀመጥ የሚገባውን ደግሞ ማስቀመጥ ነው። በሌላ አባባል በራስ ወዳድነት ላይ ያላተኮረ፣ ነገር ግን ጌታን እና ትዕዛዛቱን ማዕከላዊ ያደረገ ማከማቸት እሱ ከጌታ ጋር ማከማቸት ይባላል።

***ሀ. ለጌታ የሚገባውን መስጠት -***

ሰው ከሚያገኘው ቢያንስ አንድ አሥረኛውን እንዲሰጥ የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። ይህንን ብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን አዲስ ኪዳንም "የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ" ሲል ያዛል (ማቴ. 22:21)። ጌታ በዚህ ክፍል የእግዚአብሔን ለእግዚአብሔር አስረክቡ ሲል ለእግዚአብሔር የሚገባውን አሥራት መሆኑን ልብ ይበሉ። ሆኖም ለጌታ ቤት የሚሰጠው አሥራት ብቻ ሳይሆን ሰው በልቡ ደስ እንዳሰኘው ለጌታ ቤት ሥራ እንዲሰጥ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል።

ለ. ***የተቸገረውን መርዳት -***

ክርስቲያን በገዛ እጆቹ እየሰራ የራሱን ወጪ እንዲሸፍን የእግዚአብሔር ቃል ቢያዝም (2ኛ ተሰ 3:12)፣ በአደጋ እና በተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች የሚቸገሩትን ወንድሞች እና እህቶች እንድንረዳ እና አንዳችን ሌላችንን እንድንሸከም ያዛል (ኤፌ 4:28)። እነ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የነበሩ ወገኖች በደረሰባቸው የረሃብ አደጋ ለመርዳት ከየአብያተ ቤተክርስቲያናቱ ገንዘብ ያሰባስቡ እንደነበር ማስታወሱ ጥሩ ምሳሌ ነው። ሰው ለራሱ ብቻ ገንዘብን ቢያጠራቅም መልካም በማድረግ እና ሌሎችን በመርዳት በእግዚአብሔር ዘንድ መዝገብን ካላስቀመጠ፣ በርግጥ ያ ሰው በትኗል እንጂ አላተረፈም። ከዚህም ባሻገር 1ኛ ጢሞ 6:17-19 ያለውን ያገናዝቡ።

የተቸገረን መርዳት በጌታ ዘንድ ብድራት የአለው መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። [መዝ. (41)፡1 ምሳሌ 19፡17 መመልከት መልካም ነው።] በምሳሌ 19፡17 ላይ "ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፣ በጉነቱንም መልሶ ይከፍለዋል" ይላል።

ሐ. **ከሁሉም በላይ ራስን ለጌታ መስጠት -**

በ2ኛ ቆሮ 8:1-5 ባለው ጳውሎስ ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ሲመሰክርላቸው፣ ድሆችን ለመርዳት እና በእግዚአብሔር ቤት ሥራ ለመተባበር፣ ከአቅማቸው በላይ እንደሰጡ እና በዚህ ሥራ ለመተባበር እድል እንዲሰጣቸው እንደለመኑ ይመሰክራል። ራስን መውደድ ለሌላው የመስጠትን በረከት የሚነጥቅ ነገር ቢሆንም ራስን ከመውደድ በላይ ለጌታ እና ለሌላው ለመስጠት የሚያስችለው በመጀመሪያ ራስን የሃብት ሁሉ ምንጭ ለሆነው ጌታ

መስጠት ነው። የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ያንን ማድረግ የቻሉት በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ስለ ሠጡ ነው (2ኛ ቆሮ 8:5)። ከጌታ ጋር ለማከማቸት ራስን ለጌታ መስጠት ይጠይቃል።

## መደምደሚያ

ገንዘብ እና ሃብት ክርስቲያንን ሊያለማውም ሊያጠፋውም የሚችል ነገር ነው። ዋናው ቁልፍ ነገር አያያዙን ማወቅ እና ከጌታ ጋር ማከማቸት ነው። በእጆቹ እየሰራ ገቢውን የሚያመጣ፣ ከገቢው ለጌታ የሚገባውን የሚሰጥ፣ የተቸገሩትን ደግሞ እየረዳ እና በመልካም ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ መዝገብ የሚያስቀምጥ፣ ለነገው የችግር ጊዜ ካገኘው የሚያስቀምጥ እሱ ከጌታ ጋር አከማችቷል። ባለአደራነትን የተሞላ የገንዘብ አጠቃቀም ለጌታ ሥራ፣ ለችግረኛ እንዲሁም ለራስ በሚሆን መልኩ ገቢያችንን ማብቃቃት ነው።
የውይይት ጥያቄዎችን

1. ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር ነው የተባለው ለምድን ነው? እንዴትስ ነው የክፋት ሁሉ ስር የሆነው (1ኛ. ጢሞ 6:19)
2. በዚሁ ጥቅስ መሰረት ገንዘብን በመውደድ ገንዘብ ለማግኘት እና ለመጠቀም በመጣር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
3. ሰው ገንዘብ ወዳድ መሆኑ የሚታወቀው በምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?
4. ገንዘብ ለሰው ልጅ ዘላቂ ደስታ እና እርካታ ሊሰጠው የማይችለው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ (መክ 5:10-12)?
5. በሉቃ 12:13-21 ባለው ገንዘብን ማከማቸት ግን ለጌታ የሚገባውን አለመስጠት እና ለሌለው አለማካፈል ችግሩ ምንድን ነው?
6. በሉቃ 12:21 ላይ “ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፣ በእግዚአብሔርም ዘንድ ባለጠጋ ያልሆነ” ያለውን አንድ ቀን እንደሚበትን ይናገራል። በዚህ መሰረት
   - ከጌታ ጋር ማከማቸት ምን ማለት ነው?
   - በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ መሆን የሚቻለውስ እንዴት ነው?
7. 7. በአሥራት እና በመባ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ለጌታ አሥራት እንድናወጣ የሚያስተምረን ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥስ ምን አለ?
8. 8. በት. ሚል 3:8-12 ባለው መሰረት ለጌታ ሥራ እንድናወጣ የተሰጠንን አደራ ሳንወጣ ስንቀር የሚገጥመን ውድቀት እና አደራችንን በታማኝነት ስንወጣ የሚገጥመን በረከት ምንድን ነው?
9. 9. ከላይ በተሰጠን ምንባብ መሰረት፣ ያለንን ገንዘብ እና ሃብት እንደ ባለአደራ በሚገባ አስተርዳድረናል የሚባለው ምን ስናደርግ ነው?

# ጥናት ሦስት

**የተሰጠንን ጊዜ እንደ ባለአደራ መጠቀም**
***ዓላማ፡-***

ጊዜ እንደ ገንዘብ እና ሃብት ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሃብት እንደሆነ በማስተዋል እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ በአግባብ እንድንጠቀምበት ማሳሰብ።

*መግቢያ ፡-*

የተፈጥሮ ነገር ሆኖ ሰው ነገ እሞታለሁ፣ ያለኝ ጊዜ ያልቃል ብሎ አያስብም፣ ስለዚህም ብዙዎች ባላቸው ጊዜ አግባብ ያለው እና ተገቢ የሆነ ነገር እያደረጉበት ብርቅዬ ጊዜአቸውን ሊጠቀሙበት ሲገባ፣ ስራ ለነገ ሲያሳድሩ፣ አንገብጋቢ ነገር ተቀምጦ፣ ሲዝናኑ ይታያል። ጊዜን ለሰው እንደ ስጦታ የሰጠው እግዚአብሔር እንደመሆኑ መጠን ግን ሰው ጊዜን በአግባቡ እንዲጠቀምበት ይገባል። እንደገናም ሰው በተሰጠው ጊዜ ስለሰራው ይጠየቃል። ስለዚህም ለጊዜ ያለን አመለካከት እና አጠቃቀም እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲሆን ይገባል። በዛሬው ጥናታችን ጊዜን እንደ ባለአደራ እንዴት መጠቀም እንዳለብን እንመለከታለን።

**1) ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው።**

***ሀ.*** *ለሰው የጊዜ መጀመሪያ እና መጨረሻ አለው* - ሰማይ እና ምድር የተፈጠሩበት እና የተጀመሩበት ጊዜ እንዳለ ሁሉ ጊዜም የተጀመረበት ጊዜ እና የሚያበቃበት ጊዜ አለው። ስለ ጊዜ ጅማሬ መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን እግዚአብሔር ሰማይን እና ምድር ፈጥሮ ብርሃንን እና ጨለማን በለየበት ጊዜ የመጀመሪያ ቀን ብሎ እንደ ጀመረው እናውቃለን። ስለዚህ ሰማይና ምድር ሲፈጠሩ ጊዜም አብሮ እንደተፈጠረ እና እንደ ተጀመረ እናውቃለን። ሆኖም ግን የዚህ ሰማይ እና ምድር ስርዓት አንድ ቀን ሲያልፉ ጊዜም አብቅቶ ዘላለማዊ ሕይወት እንደምንጀመር ይታወቃል። ስለዚህ ጊዜ አሁን በምንኖረው ህይወት ራሱ ለዘላለም የሚኖር አይደለም።

**ለ.** ሰው ሁሉ የተወሰነለት ጊዜ አለው - ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው ደብዳቤ “የምሄድበት ጊዜ ደርሷል” (2ኛ ጢሞ 4፡6) እንዳለው ሁሉም ሰው ተራ በተራ ወደ ጌታ የሚሄድበት ጊዜ አለው። ሰው ሁሉ ምድራዊ ሩጫውን አስቀምጦ ነፍስ ወደሰጠው ጌታ የሚሰበሰብበት ጊዜ አለው (ዕብ 9:27) ።

ስለዚህ ጊዜን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። የጊዜም ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ጊዜ በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። ከዚህ ባሻገር ግን እያንዳንዱ ሰው ደግሞ በግሉ የተሰጠው የራሱ የጊዜ ክልል አለው። መጨረሻው ባይታወቅም፣ ሁሉም በክልል የተገደበ የጊዜ ስጦታ አለው።

**2) ሰው በተሰጠው የጊዜ ክልል ውስጥ ስለ ሠራው ስራ ዋጋ ይቀበላል**

***ሀ.*** ሰው በተሰጠው የዕድሜ ዘመን እንዲሰራው የተሰጠው *ሥራ* አለው - ከላይ በተመለከትነው የጳውሎስ ደብዳቤ፣ ጊዜው አልቆ ወደ ጌታ ሊሄድ እንዳለ ሲገልጽ፤ በነበረው ዘመን መጨረሻ የሚገባውን እንደፈጸመ ሲያመለክት “ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ፣ ሩጫዬን ጨርሻለሁ” (2ኛ ጢሞ 4፡ 4-7) ብሏል። እንዲሁም ሁሉም ሰው በራሱ ዘመን ሊሮጠው የተሰጠው ሩጫ/*ሥራ* አለው። ስለ ዳዊት እና ስለ መጥመቁ ዮሐንስ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ የሚለውን ከሐዋ 13:25፣ 36 ያስተውሉ።

**ለ.** ሰው በተሰጠው ዘመን እንደሰራው መጠን ዋጋን ይቀበላል - ጳውሎስ ሩጫዬን ጨርሻለውሁ ካለ በኋላ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል እንዳለው፣ ሁሉም በተሰጠው ጊዜ እንደሰራው መጠን ሊከፈለው ዋጋው በጌታ ዘንድ አለ። ሰለዚህ ሰው እንደማይጠየቅበት እና ዋጋ እንደማይከፍልበት ሆኖ በተሰጠው ጊዜ እንደልቡ መፈንጨት አይችልም - ጊዜውን በአግባብ እና በስርዓት እንዲጠቀም ኃላፊነት አለበት።

**3) ባለአደራነትን የሚያሳይ የጊዜ አጠቃቀም**

***ሀ.*** በመጠን መኖር - ተገቢ ባልሆነ መልኩ ሰው ጊዜን የሚያባክነው በመጠን መኖር ሲዘነጋ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው፣ ከሰማይ በታች ለሁሉም ጊዜ አለው (መክ 3:1-9)። ስለዚህም ሰው ያለውን ጊዜ አቅዶ፣ አግባብ ለሆነው ነገር ሁሉ ጊዜ ሰጥቶ ነገርን በመልክ በመልክ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል። ከሁሉም በላይ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ቃሉን የሚያነብበት እና የሚጸልይበት ጊዜ እንዲኖርረው ሲያዝ "ትጸልዩም ዘንድ እንዲቻላችሁ በመጠን ኑሩ" (1ኛ ጴጥ 4:8) ሲል ያዛል። ሰው እቅድ አውጥቶ ለሁሉም ነገር በቂ እና ምክኒያታዊ ጊዜ ሰጥቶ ከአምላኩ ጋር ጊዜ የሚያጠፋበት ሰአት ከሌለው ያ ሰው በእውነት ጊዜውን አባክኗል።

***ለ.*** *ሥራ ሰዓት አለማስቀመጥ* - ሥራ በይደር ማስቀመጥ የብዙ ሰው ችግር ነው። ነገ እሰራዋለሁ፣ ነገ እደርስበታለሁ የሚል ምክንያት መስጠት እና የግልንም ሆነ የስራ ቦታ ጉዳይ ማጓተት የተለመደ ነው። የዚህ አስተሳሰብ ችግሩ ግን ነገ የእኛ አለመሆኑን የመዘንጋት ችግር ነው። ሰው በእርግጠኝነት መናገር የሚችለው አሁን ስላለበት ጊዜ እና ሰዓት ብቻ ነው። ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ "እነሆ፣ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው" (2ኛ ቆሮ6:2) የሚለው። ማረፍ እና መዝናናት በጌታ ዘንድ የተፈቀደ ነገር ቢሆንም ሥራ በይደር አስቀምጦ መዝናናት ግን ተገቢ አይደለም። እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ሲያርፍ፣ ለስድስት ቀን የሚገባውን ሥርቶ ሲጨርስ እንደሆነ እናስተውል።

***ሐ.*** በተሰጠን ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንኑር - መጽሐፍ ቅዱስ በመጠን ኑሩ እያለ ሲያዝ፣ ከጌታ ጋር የጽሞና ጊዜ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ አሁን ባለን እና በተሰጠን ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንድንኖርም ጭምር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጌታን ባለማወቅ እና በኃጢአት የኖርንበትን ጊዜ የጨለማው ሰዓት እያለ ሲጠራው፣ ጌታን ከተቀበልን በኋላ ግን ክርስቶስን እየመሰልን እና እየለበስን የምንኖርበትን ዘመን የቀኑ ሰዓት ይለዋል። በቀኑ ሰዓት ጌታ ከእኛ የሚጠብቀው፣ እንደ ብርሃን ልጆች መልካም እያደረግን እና እንደ እግዚአብሔር ቃል እየኖርን እንድንመላለስ ነው (1ኛ ተሰ 5:1-11፣ ሮሜ 13:11-14)።

## *መደምደሚያ*

ከላይ የዘረዘርነውን አሳብ በአጭሩ ለመደምደም ጊዜ በአግባቡ እንድንጠቀምበት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእያንዳንዱ ሰው ተለክቶ የተሰጠ ስጦታ ነው። ሰው የተሰጠውን የጊዜ ገደብ በአግባብ ከመጠቀም ሌላ የተሰጠውን ጊዜ ለማራዘምም ሆነ ለማሳጠር ምንም ስልጣን እና መብት የለውም። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል የተሰጠንን ጊዜ እያስተዋልን እና እግዚአብሔርን በመፍራት እንድንኖርበት ያዛል።

የውይይት ጥያቄዎች

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ራሱ መጀመሪያ እና መጨረሻ እንዳለው በምን እናውቃለን?
2. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ግለሰብ የሰጠው የጊዜ ገደብ እንዳለ ከመጽሐፍ ቅዱስ በምን እናውቃለን?
3. በዘፍ 2:1-3 እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ ይናገራል። በዚህ መሰረት እና መክ 3:1-9 ያለውን በመመልከት እረፍት ማድረግ እና መዝናናት ለክርስቲያን ተገቢ ነው ትላለህ?
4. ጊዜን ጨምሮ ሁሉ ነገር ፍጻሜ ካለው፣ ለሰው ልጅ በዘመኑ ሊያደርገው የሚገባው ቁልፍ ነገር ምንድን ነው (መክ 12፡ 13-14 ከ መክ 12:1 ያወዳድሩ)።
5. ጊዜን ሰው አለአግባብ ተጠቅሞበታል የሚባለው ምን ሲያደርግ ነው?
6. በኤፌ 5:16 መሰረት ዘመኑን እንድንዋጅ የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። ዘመኑን የምንዋጀው እንዴት ነው?

7. በ1ኛ ተሰ 5:1-11፣ በሮሜ 13:11-14 ባሉት ክፍሎች መሰረት በመጠን እንድንኖር ያዛል። በመጠን መኖር ምን ማለት ነው? ጊዜንስ በአግባብ ከመጠቀም ጋር በምን ይገናኛል?

8. በሥራ ቦታም ሆነ በግል ጉዳይ ለዕለቱ ልናደርገው የሚገባን ነገር እያለ ሥራን በይደር አስቀምጦ ማረፍ እና መዝናናት ችግሩ ምንድን ነው?

7. ነገን መኖር እና መገኘት መቻላችንን እርግጠኛ ካልሆንን አሁን ያለንን ጊዜ እንደ ባለ አደራ መጠቀም የምንችለው እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ?

# ጥናት አራት

**የባለአደራ የግል ሕይወት**

**ዓላማ፡-**

ሁለንተናችን የጌታ ስለሆነ እንደ ባለአደራ ጌታን የሚመስል ሕይወት በሁለንተናችን መታየት እንዳለበት ማስገንዘብ።

**መግቢያ፡-**

እግዚአብሔር በአምሳሉ ሲፈጥረን እርሱ በፈቀደው መንገድ እንድንኖር ነው። እንደ ባለአደራዎች በሁለንተናችን በነፍስ፣ በመንፈስና በሥጋችን ጌታን እያከበርን የመኖር አደራ አለብን። ስለዚህ በዚህ ጥናት ጌታን ደስ የሚያሰኝ፣ ሌሎችን የሚጠቅም እና ለግለሰቡም ዕረፍትን የሚሰጥ የባለአደራነት ህይወት ምን እንደሚመስል ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

1ኛ ቆሮ. 6፡19-20 *ሥጋችን ከጌታ እንደባለአደራ የተቀበልነው መሆኑን ያመለክታል። ሐዋሪያው በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት “በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ” ይላል።* ሁለንተናቸውን እንዳስገዙ ሰዎች ለመኖር ልብ ልንላቸው የሚገቡን ነጥቦች ምንድን ናቸው? በዚህ ጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ስለሁለንተናችን የሚያስተምረንን በሙሉ መመልከት ባንችልም፣ መሠረታዊ የሆኑ ተግባራዊ ነጥቦች ላይ ግን እናተኩራለን።

### 1) ባለአደራና ልቡ [የውስጥ ማንነት]

አስቀድመን ልናተኩርበት የሚገባው ልባችን ነው። ልብን ወይም ውስጣዊ ማንነትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረን ሀሳቦች ጥቂቶቹን እንመለከታለን። ጌታን የሚመስል ህይወት እንዳለን በሌሎች ዘንድ የተገለጠ መሆን አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለልብ የሚለውና እኛ የምንለው ምን ያህል ይጣጣም ይሆን? እንደ ባለአደራ ልባችን በጌታ ፈቃድ የተሞላና ይህንኑ ለመተግበርም የሚነሳሳ መሆን አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ ልብን አስመልክቶ ችግር እንዳለብን ይናገራል። በኤር. 17፡9 “የሰው ልብ ከሁሉም ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?” ይላል። ይህ እውን ከሆነ እንደ ባለአደራ “ልቤ ምን ይመስላል?” ብለን ራሳችንን መመርመርና በጥንቃቄ መኖር ይገባል። ደግሞም በምሳሌ 4፡23 “አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና” በማለት ምክርን ይሰጠናል።

ህሊና የሚለው ቃል ከልብ የመለየቱ ጉዳይ ግራ ያጋባን ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ በጎ ህሊና እንዲኖረን አጥብቆ ያዘናል። በህሊናችን (በአይምሮችን፣ በልባችን) ምን ምን ቢገኝ መልካምና ተገቢ እንደሆነ በፊል. 4፤ 6-9 ተጽፎልናል። [በተጨማሪ ኢሳያስ 26፡3፣ ፊል. 4፡6-7፣ ዘዳግም 11፡18 ተመልከት] ስንቶቻችን ከክስ ነጻ የሆነ ህሊና (ልቦና) ይኖረን ይሆን?

መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ልብ (የባለአደራ ልብ) ምን እንደሚመስል ብዙ ምክሮችን ይሰጠናል። ከነዛ ውስጥ ጥቂት ነጥቦችን እንመለከታለን። ጌታን ደስ የሚያሰኝ የባለአደራ ልብ፣ በእውነት፣ በትህትና፣ በንጽህና፣ በትዕግሥት፣ በፍቅር እና በመሳሰሉ መልካም ነገሮች የተሞላ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

oእውነት፡- እውነትን የሚናገር ልብ መዝ. (15) 1-2

- ትኅትና፡- ትሁት የሆነ ልብ መዝ. (51)፡17፤ (131)፡ 1
- ንጽህና፡- በማዘውተር ልብን በንጽህና መጠበቅ። አቤቱ ልቤን መርምረኝ የሚል መንፈስ ይኑርህ። 2ዜና 16፡9 ማቴ. 5፡8 መዝ(139) 23፣24፤
- ፍቅርና ትዕግስት፡- የልባችን ዝንባሌ ወዴት መሆን እንዳለበት ተገልጦል። 2ተሰ. 3፡5
- የቃሉ ሙላት፡- የእግዚአብሔር ቃል በልባችን ሊሞላ ይገባል። መዝ. (119)፡11፤ ዘዳግም 11፡18

## 2) ባለአደራና አንደበቱ [ንግግር]

አንደበታችንን ለተለያዩ ነገሮች እንጠቀምበታለን። በአንዱ አንደበት እንባርካለን በዛው ደግሞ እንራገማለን። መጸሐፍ ቅዱስ የአንደበትን አስቸጋሪነት ብቻ አይናገርም፣ ምን ልናደርግ እንደሚገባንም ደግሞ ይመክረናል።

•በአንደበታችን እንዳንስት፤ እንዳንሰናከል ተመክረናል ያዕቆብ 1፡26፤ 3፡2-6፣

•ለመባረክ እንጂ ለመርገም እንዳንጠቀምበት ተመክረናል/ታዘናል። ያዕቆብ 3፡7-10 ማቴ 12፡36፣ ኤፌ 4፡25፣ 29፣

•ለሃሜት እንዳንጠቀምበት ታዘናል። ባለአደራ አንደበቱን ከዚህ ይቆጥባል። መዝ. (50)፡ 19

•አንደበትን የመግታት ፍሬ ተገልጾልናል። አንደበቱን የሚገታ ከክፉ ይጠበቃል [ምሳሌ 12፡14፣ 21፡23 መዝ 39፡1]

## 3) ባለአደራና እጆቹ [ምግባር]

ምግባራችን የሚገለጥበት አንዱ መንገድ እጃችን ነው፡፡ እጃችን በአደራ የተቀበልነው ስለሆነ ምን ያህል እንደባለአደራ እየተጠቀምንበት ይሆን? ጥቂት ምክሮችን እንመልከት።

- *ትጋት፡- ታታሪ መሆን ጌታን የማክበሪያ መንገድ ነው።* ምሳሌ 12፡14፣24፤ *ሥራ ፈት መሆን አይገባንም።* ሐዋ.20፡34፣35፡ 1ተሰ. 4፤11-12
- ንጽህና፣*ታማኝና ታታሪነት፡- ሠርቶ መብላትና የአላግባብ የነኩትን መመለስ የባለአደራ ክርስትያን ምግባር ነው።* ኤፌ 4፡28
- ለጋስነት፡- እጆቻችን የተቸገሩትን ለመርዳት ይዘርጉ። ምሳሌ 31፡20 ዘዳግም 15፡7-11፣

## 4) ባለአደራና እግሮቹ [እርምጃ]

እግር ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ እንደሚወስድ ብቻ አድርገን ልንወስደው አይገባም። እግር አረማመድን ያመለክታል። የዕለት ምግባራችን ያመለክታል። መጽሐፍ መልካም ስለሚሰሩና ለጥፋት ስለሚቸኩሉ ሰዎች ሲናገር ስለአረማመድ ይናገራል።

- መልካምን ለመሥራት የሚፈጥኑ እግሮችና ለጥፋት የሚቸኩሉ እግሮች አሉ። ሮሜ 3፡15፤ ኢሳ. 59፡7
- ለወንጌል አገልግሎት የሚነሳሱና የማይነሳሱ። [ኢሳ. 52፡7፤ ሮሜ 10፡15፣ ኤፌ. 6፡15]
- እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኝ አረማመድ ረዳት ራሱ ጌታ ነው። መዝ(119) 105፤ 56፡13፤

## 5) የባለአደራ ዓይኖቹ [ማየት]

ከዘፍጥረት ጀምሮ የምናየው አንድ እውነት የሰው ልጅ የመጀመሪያ ውድቀት “ዓይናችሁ እንዲከፈቱ . . . ሴቲቱም . . . ለዓይን እንደሚያስጎመጅ . . . አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች።” [ዘፍ. 3፡ 4- ] የተከፈተ ዓይን ሁሉ መልካምን የሚያይ አይደለም። ዓይን ስላለን ጌታ ይባረክ፣ ግን ምን እናያለን? ለሞታችን የሆነን ወይስ የህይወት ጎዳና ላይ የሚያቆመንን?

ከማየት የተነሳ የሰው የልቡ አሳብ ወደ በረከት ወይ ወደ ውድቀት ይሻገራል። ዓይን አመለካከት ወይም ባህሪን የመግለጽ ሀሳብንም አዝሎ እናገኛለን። [መዝ(19) 8፣ (131) 1 ኤፌ. 1፡18፤ ማቴ. 20፤15]

ስለዚህ ይህ ውድ የሆነው የሰውነት ክፍላችን ከማየት ያለፈ ሥራ ስላለው በማስተዋል ልንጠቀምበት ይገባል።

እንዴት አድርገን ጌታን ልናገለግልበትና ልናሳዝንበት እንደምንችል በመገንዘብ እንደ ባለአደራ ልንጠነቀቅ ይገባል። ይህ የሰውነት ክፍላችን ለሌሎችም በረከት ለራሳችንም ዕረፍትን በሚያመጣ መልኩ ልንጠቀምበት ይገባል። [ማቴ 5፡ 27-30፣ 6፡22-23፣ ምሳሌ 21፡4፣ 27፡20 ኤርምያስ 22፡17]

ወደ ጥፋት የሚዳርግህን ከመመልከት መቆጠብና እርዳታን ከሁሉን ቻይ ጌታ መለመን ማስተዋል ነው። ጌታ እንዳስተማረው ከዝሙት ሕይወት ልንርቅ ይገባል።
ከዚህም ባሻገር እግዚአብሔርን ወደመምሰል የማይመሩ ነገሮችን ለምሳሌ፡- ጥሩ መልዕክትን ያላዘሉ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ዝሙት የሚያስተምሩ ፊልሞች፣ ቪዲዮዎችን ከመመልከት በመቆጠብ ክርስቲያን ራሱን ሊጠብቅ ይገባዋል። ባለአደራነቱን የዘነጋ አማኝ እንዳንሆን የተሰጠንን ትዕዛዝና ምክር መተግበር ተገቢ ነው። [ማቴ5፡28፣ 1ዮሐ. 2፡16]

**6) ባለአደራና ጆሮው [ማዳመጥ]**

ግፍን እየሰሙ እንዳልሰሙ፣ ሃሜትን እያስተናገዱ መኖር የአንድ የባለአደራ አማኝ ሕይወት አይደለም። (መዝ. (50) 19፤ ምሳሌ 21፡13) መንፈሳዊ ትምህርትን በተመለከተ የጽድቅን ቃል የሚጠሙ እንጂ ለሥጋ ስሜቶቻችን የሚመችን ትምህርትን እየመረጥን የምንሰማ ልንሆን አይገባም። የቱን ይሆን ለመስማት የምንመርጠው? (ሮሜ 10፡17፤ ዮሐ. 5፡24፤ 2ጢሞ. 4፡3-4) መጽሐፍ ቅዱስ በያዕቆብ 1፡19-22 ስለመስማትና ስለመናገር ግልጽ የሆነ ምክርን ይሰጣል። ልብ ብለን እናንብበው እንደሚለንም እንመላለስ።

## መደምደሚያ፡-

እንደ ባለአእምሮ ልናደርገው የሚገባ ነገር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግን ጌታን ለማስከበርና ለሌሎች ለመትረፍም ስንል ልንሰራ ፤ልንተጋ ይገባል።
እንደ ባለአደራ እርሱን እየመሰሉ በማይመላለሱ አማኞች ጌታ ደስ አይሰኝም። ስለዚህ በሥርዓቱ እንመላለስ፤ ራሳችንንም በጸጋ ጥላ ሥር እንጣል። [1ቆሮ. 6፡9-10፣ 13-18፣ 7፡1-8፤ 2ሳሙ11፡2-5፣ 14-17፣ 26-27]

መጸሐፍ ቅዱስ ሁለንተናችንን ስለሚፈውስና እረፍት ስለሚያመጣልን ነገር ሲናገር የከበሩ ነገሮችን እንድናስብ፤ ልባችሁን በቅዱስ ቃሉ እንድን ሞላ ይመከረናል። [ፊል. 4፡8 መዝ. 119፡28፣ 11፣37፣38፤ ሮሜ 6፡11-13፤ 1ተሰ. 4፡3-5፤ 5፡22] ጤናማ ህይወት ይኖረን ዘንድ ራሳችንን ለነዚህ እውነቶች እናስገዛ።

እንደባለአደራ ንጹህ የሆነውን ኑሮ አንዳትኖር ምን ይሆን የሚያሰናክልልህ? ምንስ እርምጃ እየወሰድክ ነው ደስ ልታሰኘው? የጌታ ምህረቱ ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው። ጸጋውም በቂ ነው። ስለዚህ ድልን ወደሚሰጥህ ሁሉን ቻይ ጌታ ተመለስ።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በ1ኛ ቆሮ. 6፡19-20 ስለሥጋችን (ሁለንተናችን) የተጠቀሱ መሠረታዊ ነጥቦች ምንድን ናቸው? በሥጋችን ምን እንድናደርግ ነው የታዘዝነው?
    - ቁልፍ ቃላት፡- የተቀበላችሁት፣ ተገዝታችኋል፤ አይደላችሁም፣ አክብሩ
2. ሁለንተናችንን ስንል ምን ምንን ያካትታል ትላለህ?

3. የሰው የውስጥ ማንነቱ ከልብ ጋር የተያያዘ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለልብ በኤር. 17፡9 የሚናገረውን ተወያዩበት? ከዚህ አንጻር ስለራስህ ምን ትላለህ?

4. በምሳሌ 4፡23 ልባችንን በተመለከተ የታዘዝነው ምንድን ነው? ለምን?

5. በምሳሌ 4፡23 የተረዳህው መረዳት ከማቴ. 15፡14፣ 18-20 ጋር እንዴት ይያዛል? ከነዚህ ጥቅሶች እንደባላደራ የተረዳህውን ለቡድንህ አካፍል።

6. መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ባለአደራ ለመኖር ጠቃሚ ምክሮችን ይሰጠናል። ልብን አስመልክቶ ከሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ምን ትገነዘባለህ?
   - ❖ስለእውነት፡- በመዝ. (15) 1-2
   - ❖ስለትኅትና፡- በመዝ. (51)፡17፤ (131)፡ 1
   - ❖ስለንጽህና፡- በ2ዜና 16፡9 ማቴ. 5፡8 መዝ(139) 23፣24፤
   - ❖ስለፍቅርና ትዕግስት፡- በ2ተሰ. 3፡5
   - ❖ስለቃሉ ሙላት፡- በመዝ. 119፡11፤ ዘዳግም 11፡18፣
   - ❖ስለምናስበው፤ በፊል 4፡6-8 ኢሳያስ 26፡3፣ ዘዳግም 11፡18

7. እንደባለአደራ አንደበታችንን እንዴት ነው የምንጠቀምበት?
   - በያዕቆብ 1፡26፤ 3፡2-6 ምን ተመክረናል?
   - አንደበታችንን ስለምንጠቅምባቸው ሁኔታዎችስ?
   - ያዕቆብ 3፡7-10
   - ኤፊ 4፡25፣ 29
   - ማቴ 12፡36፣
   - አንደበትን የመግታት ጥቅምና ፍሬ ምንድን ነው? ምሳሌ 12፡14፣ 21፡23 መዝ (39፡1)

8. ጌታን በሁለንተናው እንደሚያገለግል አማኝ ራስህን ስትመለከት፣ እጅህን እንዴት ነው የምትጠቀምበት? ከሚከተሉት ቃላቶች አንጻር ተወያዩባቸው።
   - ❖ትጋት፡- ምሳሌ 12፡14፣24፤
   - ❖ሥራ ፈትነት፡- ሐዋ.20፡34፣35፡ 1ተሰ. 4፤11-12
   - ❖ንጽህና፣ታማኝና ታታሪነት፡- ኤፌ. 4፡28
   - ❖ለጋስነት፡- ምሳሌ 31፡20 ዘዳግም 15፡7-11፣ መክ. 9፡10

9. እግሮችህ ወዴት ይፈጥናሉ? እንዴትስ ነው የምትጠቀምባቸው?
   - ❖ተግባር አስመክቶ፡- ከሮሜ 3፡15፤ ኢሳ. 59፡7 ትማራለህ?
   - ❖ወንጌልን አስመልክቶ፡- ከኢሳ. 52፡7፤ ሮሜ 10፡15፣ ኤፌ. 6፡15 ምን ትረዳለህ?
   - ❖ረዳትን ለማግኘት፡ ከመዝ(119) 105፤ (56)፡13፤ ማን ነው ረዳት ወይም ምን ያስፈልጋል?

10. 10.በመጽሐፍ ቅዱስ “ዓይን” የሚለው ቃል ከብልቶቻችን አንዱ ከመሆን ሌላ ምን ትርጉም አለው? መዝ (19) 8፣ (131) 1 ኤፌ. 1፡18፤ ማቴ. 20፤15

11. 11.ዓይን እንደ ብልት ያለው ሥራንና ከዛ ውጪ ያለውን ትርጉም በማነጻጸር በስነምግባራችን ላይ ስለአለው ተጽዕኖ ተወያዩበት።

ከሚከተሉት ጥቅሶች አንጻር እንደባላደራ ምን ልታደርግ ይገባል?

- ዘፍ. 3፡ 4- ማቴ 5፡ 27-30፤ 6፡22-23፤
- ምሳሌ 21፡4፤ 27፡20 ኤርምያስ 22፡17

12.ጆሮቻችንን እንዴት ነው የምንጠቀምባቸው? ከሚከተሉት ጥቅሶች የምትረዳውን ለቡድንህ አካፍል።

- ፍርድን አስመልክቶ፡- ምሳሌ 21፡13
- መንፈሳዊ ትምህርትን በተመለከተ፡- ሮሜ 10፡17፤ ዮሐ. 5፡24፤ 2ጢሞ. 4፡3-4
- መስማትና መናገር በተመለከተ፡- ያዕቆብ 1፡19-22

# ጥናት አምስት

**ባለአደራና የጸጋ ስጦታዎች**

***ዓላማ፡-***

የጸጋ ስጦታዎች ባለአደራው በታማኝነት ሰጪውን ሊያከብርባቸውና ሌሎችን በቅንነት ሊያገለግልባቸው እንደተሰጡት ማስገንዘብ።

***መግቢያ፡-***

የጸጋ ስጦታዎቻችን ሆኑ የተፈጥሮ ችሎታዎቻችን ባለአደራነት የተሰጡን ስለሆኑ በታማኝነት ጌታንና የርሱ የሆኑትን ልናገለግልባቸው ይገባል። በዛሬው ጥናታችን ስጦታዎቻችንን በመለየት እንደ ባላደራ ታማኝ ሆነን ኀላፊነታችንን እድንወጣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን እንመረምራለን።
ስጦታዎቻችን ሁሉ ባለቤት እንዳላቸው መገንዘባችን እንደ ባለአደራ በትጋትና በታማኝነት እንድናገለግል ያደርገናል። በተጨማሪ አለማገልገላችን ጌታን እንደማያስከብር፣ የሌሎችንም ልብ እንደማያሳርፍም እንገነዘባለን። እንደ ባለአደራ አለማገልገል በግል ህይወታችን በረከትን፣ ዕድገትንና ዕረፍትን በሙላት እንዳናገኝ ያደርገናል።
በመክሊታችን እናገልግል። ለመክሊቱ ባለቤት በመክሊቱ ያልሠራ/ያላተረፈ በመጨረሻ መልስን ይሰጣል (ማቴ. 25፡14-30)። ሐዋሪያው ጴጥሮስ በመልዕክቱ (በ1ጴጥ. 4፡10) እንደ ደጋግ መጋቢዎች በጸጋ ስጦታዎቻችን በትጋት እንድናገለግል ይመክራል።
ይህን ባለማድረግ ከታቀደልን የከበረ ነገር ከመጉደል ጌታ ይጠብቀን። ከዚህ አይነት ህይወት ለመጠበቅ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ እንበል።

### 1) *የጥሬ ቃል ትርጉም፡- የጸጋ ሥጦታዎች*

"ጸጋ" የሚለው ቃል ከጌታ ቸርነት የተነሳ ስለሚሆንልን ነገር ያመለክታል። "ስጦታ" የሚለው ቃል ደግሞ የሌለንን ወይም የኛ ያልሆነ ነገርን ያመለክታል። ስለዚህ ስለ "ጸጋ ስጦታዎች" ስናስብ የእኛ ስላልሆኑ ነገር ግን በጌታ ቸርነት በአደራነት ስለተሰጡን ክቡር ነገሮች ነው የምናስበው። ስጦታ ሰጪ አለው፤ ሲሰጥም ምክንያትና ዓላማ አለው።

### 2) *ዓላማቸውና የሰጪው ልብ፡-*

ልባም ባለአደራ የተሰጠው ነገር ኃላፊነት እንዳለበት፤ የራሱ ነገርም እንዳይደለ የሚገነዘብ ነው። የጸጋ ስጦታ ባላደራ የባለቤቱን ልብና በስጦታው ምን ማድረግ እንዳለበት በቂ የሆነ መረዳት ይኖረው ዘንድ ይገባል።
የጸጋ ስጦታን የሰጠን ጌታ የልቡ አሳብ ፍቅር፣ ርኅራኄ፣ ጽድቅና የመሳሰሉት የሞላበት ነው። ከእንደዚህ አይነት ልብ የመነጩ ስጦታዎች የተሰጡት ቅዱሳን እንዲታነጹበት ነው። (ኤፌ. 4፡ 6-13፤ 1ቆሮ. 12፡27) የጌታ የልቡ አሳብ እንዲሞላ እንደ ታማኝ ባለአደራ ምዕመናንን ወደ ክርስቶስ ሙላት እንዲደርሱ በስጦታችን እናገለግል።

### 3) *የስጦታዎቹ ማኅበራዊና ግላዊነት*

ከሁለት ምክንያቶች የተነሳ ስጦታዎቻችን አያስታብዩንም። ምናልባት የመታበይ ችግር ካለብን፣ ሊያስታብዩንም አይገባም። አንደኛ ባለቤት አላቸው። ሁለተኛ ከዓላማቸው አንጻር ማኅበራዊ እንጂ ለግል ጉዳይ የተሰጡ አይደሉም። ስለዚህ የጸጋ ስጦታዎች የባርያነት ወይም የአገልጋይነት መንፈስን እንጂ የሚታበይ የሹምነት መንፈስን በውስጣችን አያነሳሱም። የትዕቢት ችግር ከሌለብን በስተቀር።
ባለአደራ፡-

፩ኛ. በኤፊ. 4፡ 8-16 ክርስቶስ ስጦታዎችን የሰጠው አካሉን እንዲያንጽበት ነው። አሠራሩም በፍቅር ነው። ስለዚህ ባላደራ በፍቅር የጌታን ማኅበር ለማነጽ በተሰጠው ጸጋ ይተጋል።

፪ኛ. በሮሜ 12፡3-8 የጸጋ ስጦታዎችን የተቀበለው እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ በትዕቢት እንዲሞላ አይደለም።

የጸጋ ስጦታዎቹ የተሰጡት አካሉን በባለአደራነት ለማገልገል ነው ስለዚህ ታማኝ ባላደራ ውስጡን ከእኔነት መንፈስ ወይም ከሰዎች ግፊት የተነሳ የማይገባውን ሥፍራን ለራሱ ከመውሰድ ህይወት ራሱን ይጠብቃል።

**4) የባለአደራ ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት፡-**

የጸጋ ስጦታን ከጌታ የተቀበለ በ1 ቆሮ 13 እንደተገለጸው ከስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠውን ፍቅርን በመያዝ፣ በታደሰ አእምሮ ሚዛናዊ አገልግሎትን ይሰጣል። በጸጋ የሚያገለግል የሚል ምን ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ፍሬዎች የተሞላና በዛ የሚመላለስ መሆኑ የሚመሰከርለት ነው። የመንፈስ ፍሬዎች በህይወቱ እንዲበዙ ጌታውን በመማጸን፤ ምሳሌያዊ ህይወትን ሁሌ ይናፍቃል።
ሚዛናዊ ሕይወት ስላለው ስጦታውን ሳይጠቀምበት እንደው ዝም ብሎ አይመላለስም። የተሰጠውን አደራ በጥበብ፣ በቅድስና፣ በትህትና፣ በመሰዋዕትነትና በእግዚአብሔር ፍርሃት ሊወጣ ራሱን ይሰጣል።
1ተሰ. 2፡10

**5) የእግዚአብሔር ፍርሀት፡-**

የባለአደራ የጸጋ አገልግሎት ፈሪሃ እግዚአብሔር በራሱና በሚገለገሉት ላይ ሊፈጥር ይገባል። ንጹህ አገልግሎት አገልጋዩን ከሚገባው በላይ ክብርን ለራሱ እንዳይፈልግ ያደርገዋል። የሚያገለግላቸው ስለእርሱ ያላቸው መረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይሆን ዘንድ በየዕለቱ አረማመዱንና የአገልግሎቱን ንጽህና በደንብ ይመዝናል። ለምዕመናኑም በተሰጣቸው ጸጋ በጌታ ፍርሃት፣ በታማኝነት፣ እንደ መልካም ባለአደራ እንዲያገለግሉ ምሳሌ ይሆናል። 1ጢሞ. 4፡11-17

**6) የባለአደራ ስጦታ አጠቃቀም፡-**

a. ስጦታዎቻችንን በሚከተሉት ነጥቦች አንጻር መጠበቅ መልካምና ፍሬያማ ነው።
b. ረብን ባለመፈለግ ይጠቀምበታል። ማቴ 10፡8 1ተሰ. 2፡ 6
c. በምስጋና መንፈስ የጠቀምበታል። ከቅዱስ ጌታ ስለተቀበልነው ቅዱስና ክቡር የሆነ ስጦታ ለዚህ ያበቃኸኝ እኔ ማን ነኝ በማለት ማመስገን ይገባል።
d. በጽድቅና በእውነት። ምድራዊ አሳብን ሳይደባልቅ ጌታውን ያገለግላል።
e. መክሊቱን አይቀብረውም ያተርፍበታል እንጂ። በፍጹም ጸጋውን አይቀብርም። ከተጠቀመበትም ለጌታ ክብር ያተርፍበታል እንጂ ለዝናና ራስን ለማደላደል አያውለውም። ማቴ 25፡ 14-30
f. በመንፈሳዊ ህይወቱ ያድግበታል። ከጌታ ጋር በመሆን የበረከት ተካፋይ ብቻ ሳይሆን የጌታን ማንነት በመረዳት ራሱን ላቅ ወዳለ ደረጃ ያደርሳል። ከጥቂት ብዙ እንደሚሰበሰብ በህይወቱ ይማራል። (በአምስት አምስት ሺ መመገብ፤ ከሰባት አስራሁለት መሶብ እንደሚሰበሰብ ትምህርትን ያገኛል። ማር. 8፡1-8)
g. ጌታው እንደሚመለስ በማሰብ በታማኝነት ያገለግላል። 1ጴጥ. 4፡7-11፤ 2ጴጥ. 3፡14፤ ራዕይ 22፡12
h. በጸሎት መንፍስ ያገለግላል በቈላ. 3፡17።

**7) የተፈጥሮ ችሎታዎችን መጠቀም**

ሁለንተናችን የእርሱ ስለሆነ የተፈጥሮ ችሎታዎቻችን ሆኑ ተምረን የቀስምናቸው ሞያዎቻችን የጌታ ናቸው። በትክክል ስንጠቀምባቸው፣ የተፈጥሮ ችሎታዎቻችችን ለጌታ ክብር ይውላሉ። ሌሎችንም ያሳርፋሉ። በብሉይ ኪዳን ጌታ ባስልኤልን በሞያ ለዓላማው እንዴት እንደለየውና እንደተጠቀመበት እንመለከታለን። ያለንን ችሎታዎች ጌታ ለክብሩ ይጠቀምባቸዋል።
እንደ ባለአደራ ችሎታዎቻችንን ለክብሩ እንድንጠቀምባቸው ጌታ ይርዳን። በቈላ. 3፡17 ላይ "የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ስም አድርጉት" ይላላል። ይህ አባባል በተግባራችሁ ሁሉ እርሱን አስገቡ ማለቱ ነው። በዛም እርሱን አክብሩት ማለት ነው።

# መደምደሚያ:-

አማኞች በሙሉ የጸጋ ስጦታን ከጌታቸው ተቀብለዋል። ለአማኝ የጸጋ ስጦታ የተሰጠው በዘመኑ ሊያተርፍበትና ጌታውን ሊያስከብር ነው። የጸጋ ስጦታዎቹን እንደሚገባ ለመጠቀም ጉልበት ወደ ሚሆነው ጌታ ዙፋን አዘውትሮ ይመጣል። ትዕቢት እንዳይገዛውም ራሱን ለመጸሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ያስገዛል። በተጨማሪም የሚያገለግላቸው ባላደራነቱን ተመልከተው የሚሰጡት ሥፍራ በጌታ ቃል ሲመዘን ተገቢውን ብቻ እንዲሆን ያስተምራል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. 1.መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ባለአደራ በስጦታዎቻችን እንዴት እንድንጠቀም ነው የሚያስተምረን? (ማቴ. 25፡14-30፤ 1ጴጥ. 4፡10)

2. 2.ጌታ ስጦታዎችን የሰጠበት ዓላማ ምንድን ነው? (ኤፌ. 4፡ 6-13)

3. 3.በሮሜ 12፡3-8 ባለአደራ የተቀበላቸውን የጸጋ ስጦታዎች በምን መንፈስ ነው እንዲይዛቸው የተመከረው?

4. 4.በ1 ቆሮ 13 እንደተገለጸው ከስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠው ምንድን ነው? እንዴትስ ነው ከ ሮሜ 12፡3-8 ጋር የሚለየው? እንዴት ነው የጸጋ ስጦታዎቻችን እንደ ባለአደራ በአግባብ እንድንጠቀምባቸው የሚረዳን?

5. 5.የባለአደራ ሚዛናዊ የአገልግሎት ህይወት ምን ይመስላል ትላለህ? በ1ተሰ. 2፡10 ስለ ባለአደራ ሚዛናዊ የህይወት ልምምድ ምን ተገልጦል?

6. 6.አንድ ታማኝ ባለአደራ በምን አይነት መንፈስ ነው ማገልገል ያለበት? በሚከተሉት ነጥቦች አንጻር ተወያዩባቸው።
    - •ረብን በተመለከተ ምን ያደርግ ዘንድ ይገባዋል?   ማቴ 10፡8 1ተሰ. 2፡ 6
    - •መክሊቱን እንዴት ይጠቀማል?  ማቴ 25፡ 14-30
    - •በ ማር. 8፡1-8 ካለው የጌታ ታምር ሐዋሪያት ስለ አገልግሎታቸው ምን የተማሩ ይመስልሃል? አንተስ ምን ትማራለህ?
    - [ከጌታ ጋር ከጥቂት ብዙ እንደሚሰበሰብ። በአምስት አምስት ሺ መመምገብ፤ ከሰባት አስራሁለት መሶብ እንደሚሰበሰብ ትምህርትን ያገኛል። ]
    - •የወደፊቱን ሲያስብ በምን መንፈስ ያገልግላል?
    - •አገልግሎቱን በምን ይመሰርታል? በቈላ. 3፡17

# ጥናት ስድስት

**ባለአደራና የሥራ መስክ**

**ዓላማ፡-**

አንደ አማኝ በተሰማራበት ሥራ እንደባለአደራ፤ በታማኝነትና በትጋት በመሥራት ጌታውን ሊያስከብር እንደሚገባ ማስገንዘብ።

*መግቢያ፡-*

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው ምድርን እንዲንከባከባት፣ በሥራ እንዲጠመድ አድርጎ ነው። ሁሉን ሙሉ አድርጎ በፈጠረባት በገነት አባታችን አዳም ከተሰጠው አደራ አንዱ ሥራን መሥራት ነበር። (ዘፍ. 1፡26፤ 2፡5፣ 15) ከውድቀት በኋላ ለመኖር የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በሙሉ ከዛ የተለዩ አይደሉም። የምንሠራው ሥራ በእግዚአብሔር ቃል እውነት ሲመዘን ምን ያህል ሚዛንን የሚደፋ ነው? ጌታ ኢየሱስ ቢሆን የሚሠራውን ሥራ ነው ወይ የምንሠራው? እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ በተሰማራንበት ሥራ እንደ ባላደራ በመሆን ጌታን ማስከበርና ሌሎችን ማሳረፍ እንችላለን።

በዛሬው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ ሥራን አስመልክቶ የሚያስተምረንን መጠነኛ እውነቶችን በመውሰድ ስለሥራ ሚዛናዊ የሆነ አመለካከትን እንጨብጣለን።

## 1) ሥራ በኛላይ የተጨመረ ዕዳ አይደለም

እግዚአብሔር ሲፈጥረን ምድርን ልንገዛና ልናበጃጃት ነው። ከውድቀት በኋላ ሥራ አልቆመም ወይም አይ አበሳዬ የምንለው ነገር ሆኖ አልቀረበልንም። ሥያሜውን ለእንጀራ ወይ ለአገልግሎት ወይም ሌላ በማለት ብንለያየውም፣ ሁላችንም እንሠራልን። (ዘፍ. 1፡26፣ 2፡5፣15) ጥያቄው ምን አይነት ሥራ፣ ደግሞስ እንዴት ነው የምንሠራ የሚል ነው።

## 2) የሥራ አይነቶችና ባለአደራ

ሰው ሁሉ ይሠራል። አንዳንዶች ኑሮን ለማሸነፍ በተለያዩ የሞያ መስክ ተሰማርተዋል፣ ሌሎች በትምህርት ተጠምደዋል አንዳንዶች ደግሞ ጥሪ ደርሷቸው ለወንጌል ሥራ ራሳቸውን ለይተዋል።

ምንም እንኳን በወንጌል ሥራ ጥላ አንዳንዴ አሳዛኝና ጌታን የማያስከብሩ ነገሮችን ብናይም፤ የወንጌል ሥራ በግልጽ ጌታን የሚያስከብር ነው። የተቀሩት የሥራ ዓይነቶችስ? በማንኛውም የሥራ መስክ እንደ ባለአደራ በትጋትና በታማኝነት መሥራት እንደሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ይህን በማድረግም ጌታን እናከብራለን።

## 3) ባለአደራ ሥራን የሚሠራበት መንፈስ

የሚከተሉት ነጥቦች ሥራችንን ስንሠራ ምን አይነት መንፈስ ሊኖረን እንደሚገባ መጠነኛ አሳብን ይሰጡናል።

a) መልካም ሥራን ለመሥራት እንደተፈጠረ በመረዳት ይሰራል።
b) “እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ፈጠረን።” በማለት ጳውሎስ በኤፌ 2፡10 አዲስ ፍጥረት የሆን ነው ለከበረ ነገር መሆኑን ይናገራል
c) ልቡን ዘላለማዊነት ላለው፣ ለማይጠፋው ለመሠራት ያዘጋጃል። (ዮሐ. 6፡27) ጌታ በዚህ ክፍል ስለደኅንነት እየተናገረ ቢሆንም፣ የዕለት ኑሮችንን ከማሸነፍ የላቀን ነገርን በልቦናችን እያሰላሰልን ልንሠራ እንደሚገባም ያመለክታል።
d) 3.ከምድራዊው ነገር ያለፈን የሰማዩን እያሰላሰለ ይሠራል። ቈላ. 3፡1-3
e) 4.ጌታውን ይታመናል ቢሆንም የዕለት ኑሮን ለማሸነፍ ይሠራል። ማቴ. 6፡19-34
f) 5.ለትጋት እንጂ ለስንፍና ሥፍራ አይሰጥም። ምሳሌ 6፡6-11፤ 12፡11፣ 24፣ 27፤ 27፡22፤ 28፡19
g) 6.የትጋትንና የስፍናን ልዩነት በደንብ ያጤነ ነው። መክ. 4፡5፤ ምሳሌ 21፡25፤ 24፡30-34

h) 7.በሥራ መድከሙን ለደስታው እንጂ ለማጉረምረም ምክንያት አያደርግም። መክ. 2፡24፤ 3፡22
i) በዕቅድና በፕላን ይሰራል። ምሳሌ 21፡5
j) ኑሮውን ለማሸነፍና ለወገኖቹ ለመትረፍ ይሠራል። 1ጢሞ. 5፡8፣ 2ተሰ. 3፡10-13

## መደምደሚያ፡-

የጌታውን ልብ የሚያሳርፍ ባለአደራ ሥራን እንደው የአርባቀን ዕድሌ በሚል መንፈስ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠው ታላቅ ስጦታ እንደሆነ በመቁጠር በደስታ ይሠራል። ኑሮን ለማሸነፍና ለመሻሻል መሥራት ተገቢና እንደ ባለአይምሮ ልናደርገው የሚገባ ነገር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግን ጌታን ለማስከበርና ለሌሎች ለመትረፍም ስንል ልንሰራ ይገባል።

በመክ. 2፡24 “ለሰው . . . በድካሙም ደስ ከሚለው በቀር የሚሻለው ነገር የለም፤ ይህም ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅ እንደ ተሰጠ አየሁ” ይላል። ስለዚህ አማኞች በትጋት ልንኖርና በዛም ደስ ልንሰኝ ይገባል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ሥራ እንዴት ነው የተጀመረው? በምንስ መንፈስ ነው ሥራን ልንቀበል የሚገባን? (ዘፍ. 1፡26፤ 2፡5፣ 15)
2. በኤፌ 2፡10 ላይ ስለ ሥራ ምን ይናገራል? ይህ ምን ያህል ከምንሰራቸው ሥራዎች ጋር ይያያዛል?
3. የትጋትና ስንፍና ንጽጽር፤
    - በረከትና ድህነት በማን እጅ ናቸው? ምሳሌ 12፡11፤ 28፡19፤ ምሳሌ 6፡6-11
    - የትጉና የታካች ፍሬዎች በምን ይለያያል? ለምን? ምሳሌ 12፡24፣ 27፤
    - በምሳሌ 27፡22 መሰረት ከስንፍና ለመውጣት ምን ያህል ቀላል ነው? ለምን?
    - ከተመለከትናቸው ጥቅሶች እንደ ባለአደራ ለአንተ የሚሆን ምን ትምህርት አገኘህ? ውሳኔህስ ምንድን ነው?
4. ከመክ. 4፡5፤ ምሳሌ 21፡25፤ እና ምሳሌ 24፡30-34 በመመልከት፡-
    - ትጋታችንን አስመልክቶ የምንማረው ትምህርት ምንድን ነው?
    - አንተን በየትኛ ቡድን ታየዋለህ?
    - ወደ ላቀው ለመሻገር እና በዛ ለመቀጠል ምን ታደርጋለህ?
5. መጸሐፍ ቅዱስ በሥራ መድከማችንን እንዴት አድርገን እንድንመለከተው ነው የሚያበረታታን? መክ. 2፡24፤ 3፡22 የዕለት ሥራህን ስታስብ ለደስታህ/ምስጋና ወይስ ለማጉረምረም ምክንያት ነው የሚሆንህ?
6. በምሳሌ 21፡5 በዕቅድና በፕላን ስለመሥራት ምን ያስተምረናል?
7. ሥራን ስናስብ ትጋታችን እስከምን ድረስ ነው መሆን ያለበት? ሥራን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የማይደግፈው ጉዳይ ምንድን ነው? 1ጢሞ. 5፡8፣ 2ተሰ. 3፡10-13፣ ምሳሌ 13፡22
8. በሥራ መስካችን እንዴት ነው ሥራችንን ልንሰራ የሚገባን? ቈላ. 3፡1-3
9. ጌታን መታመንና በሥራ መትጋት ምን መመሳሰልና ልዩነት አላቸው? ኑሮን ለማሸነፍ መትጋትና እምነት ምን መለያየትና መዛመድ አላቸው? ማቴ. 6፡19-34፤ ምሳሌ 6፡6-11
10. ስለ ሥራ ያለህን አመለካከት በተመለከተ ከዛሬው ጥናት ምን ተማርክ? ልታስተካክለው የሚገባህ ነገር ካለ፤ ለማስተካከል ምን እርምጃን ትወስዳለህ?

# ጥናት ሰባት

**ክርስቲያንዊ ኅብረትን እንደ ባለአደራ መጠበቅ**

***ዓላማ፡-***

አማኞች እንደ ባለአደራ ዘወትር ኅብረት ማድረግ እንደሚገባን እና አንድነትን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለን ማሳሰብ።

***መግቢያ***

*ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከእግዚአብሔር የተሠጡን ሥጦታዎች እንደሆኑ አስበው ያውቃሉ? እግዚአብሔር ለበረከት አድርጎ የሠጠንን ሰዎችስ የመጠበቅ አደራ እንዳለብን ትኩረት ሰጥተው ያውቃሉ? ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሌሎች ሰዎችንም ግንኙነታችንን እንደ እግዚአብሔር ቃል በመንከባከብ እንድንጠብቅ ለእኛ ኃላፊነት ተሰጥቶናል።*

**1) እግዚአብሔር ኅብረትን ይወዳል።**

ኅብረትን ለሰው ልጅ የሰጠው እግዚአብሔር ከመሆኑ ባሻገር እግዚአብሔር ኅብረትን የሚወድ እና ለኅብረት ትኩረትን የሚሰጥ አምላክ መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን። እግዚአብሔር ኅብረትን ስለሚወድ በኅብረት ውስጥ በረከትን ከማስቀመጡ ሌላ ያለ ኅብረት መመላለስ ትርፉ ጉዳት እንደሆነ በአጽንኦት ይናገራል (መዝ 133:1-4፣ መክ 9:4)።

ሀ. በሥላሴ ውስጥ ኅብረት አለ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ መሆኑን አስረግጦ ያስተምራል (ዘዳ 6:4-6)። ስለዚህም እግዚአብሔር አንድ መሆኑን እናውቃለን። ነገር ግን ስለ አንዱ እግዚአብሔር ስናስብ ሁሌም በኅብረት እና በአንድነት የሚገኙ ሶስት ሰብዕናዎች (አብ ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ) እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ ሦስቱም ሰብዕናዎች በኅብረት አብረው የሚሰሩ (ኤፌ 1:3-11)፣ በአንድነት ኅብረታቸውን ጠብቀው የሚኖሩ እንደሆነ ያስተምረናል (ዮሐ 10:30፤ 17:20-23)። ስለዚህም እግዚአብሔር የኅብረት ሁሉ ጀማሪ ብቻ ሳይሆን፣ የጤነኛ ኅብረት እውነተኛ ምሳሌ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ለኅብረት ነው።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ፣ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ አልፈቀደም (ዘፍ 2:18-19)። ስለዚህም እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን በመስጠት የቤተሰብን ኅብረት እንደጀመረ ከቅዱስ ቃሉ እንማራለን። ነገር ግን በቤተሰብ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ በምንም ነገር ለሰው ብቸኛ መሆን መልካም አይደለም (መክ 4:7-12)።

ሐ. የክርስቲያን ኅብረት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው።

ሰው ከማንኛውም ሰው ጋር በተለያየ መልኩ ኅብረት ሊኖረው ይችላል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ሁለት አብይት ኅብረቶችን ስጥቶናል። አንደኛው ከእግዚአብሔር ከራሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ከአማኝ ወገኖች ጋር ኅብረት ማድረግ ነው (1ኛ ቆሮ 1:9፣ 1ኛ ዮሐ 1:3-4)። ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ራሱ ትክክለኛው ትርጉሙ ከዓለም በክርስቶስ ተጠርተው የመጡ አማኞች ኅብረት ማለት ነው። በዚህ ጤነኛ ኅብረት መካከል እግዚአብሔር ሁሌም ይገኛል። በእንደዚህ አይነቱ ኅብረት ውስጥ ወገኖች በኅብረት የሚለምኑትንም ጌታ ይሰማል (ማቴ 18:18-20)። እንግዲህ ይህ ኅብረት ከጌታ የተሰጠ እንደመሆኑ፣ አማኞች ደግሞ በምላሹ፣ የተሰጣቸውን ኅብረት እንደሚገባ ሊንከባከቡት ይገባል።

**2) *ኃጢአት የኅብረት ጠንቅ ነው።***

ኅብረት በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ፣ በእግዚአብሔር የተሰጠ መልካም ነገር ሆኖ ሳለ፣ ሰው በጥንቃቄ ካልያዘው በኃጢአት በበደል ምክንያት ሊበላሽ የሚችል ነገር ነው። ለዚህም ነው አማኝ ከእግዚአብሔርም ጋር ሆነ

ከሌላው ወገን ጋር ያለውን ኅብረት እንደ ባለአደራ ተጠንቅቆ ሊይዘው የሚገባው። ከዚህ በታች ያሉት ነጥቦች ኃጢአት ኅብረትን እንዴት እንደሚያበላሽ ሊያመለክተን ይችላል።

ሀ. ኃጢአት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ያበላሻል።

አዳም እና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን መልካም ኅብረት ያበላሹት እና የተደበቁት ኃጢአትን በማድረጋቸው ነው (ዘፍ 3:1-8)። ዛሬም እንደ ክርስቲያን ሕይወታችንን በሚገባ እየጠበቅን መኖር ካልቻልን እና በኃጢአት እና በጨለማ የምንመላለስ ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መልካም ኅብረት እናበላሻለን (1ኛ ዮሐ 1:5-6)።

ለ. ኃጢአት በቤተሰብ ውስጥ ያለውን መልካም ኅብረት ያበላሻል

እግዚአብሔር በመጀመሪያው ቤተሰብ ውስጥ የሰጠው ኅብረት የተበላሸው ኃጢአት በዚያ ቤተሰብ ውስጥ ከገባ በኋላ እንደሆነ ከዘፍ 3 እናውቃለን። ከዚያም በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘሩት ብዙ ቤተሰቦች ውስጥ ኃጢአት እና መበዳደል የብዙ ቤተሰቦችን ቤት እንዳበላሸ እና እንደበጠበጠ ከሚከተሉት ክፍሎች እንማራለን (አቤል እና ቃየን ዘፍ 4:1-9፤ የይስሐቅ ቤተሰብ ዘፍ 27፤ የያዕቆብ ቤተሰብ ዘፍ 47-50 እንዲሁም የዳዊት ቤተሰብ 2ኛ ሳሙ 13-14)።

ሐ. ኃጢአት ክርስቲያናዊ ኅብረትን ያበላሻል

አንድ ልብ ማጣት፣ ጥላቻ፣ ቅራኔ፣ ወገንን መበደል … የመሳሰሉት ነገሮች የኅብረት እና የአንድነት ጠንቅ ናቸው። የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ምንም እንኳ በብዙ የመንፈሳዊ ስጦታዎች በረከት ባለቤት የነበረች ብትሆንም፣ በዚያ ኅብረት ውስጥ የነበረው መከፋፈል እና ኃጢአት የቤተክርስቲያኒቱን አንድነት የነቀነቀ ነበር (1ኛ ቆሮ 1፡ 10-15)። ስለዚም ነው ብዙ የጳውሎስ መልዕክቶች፣ እንድንተሳሰብ፣ በአንድ ልብ እንድንሆን፣ መከፋፈልን ከመካከላችን እንድናርቅ የሚመከሩን(ፊል 2:1-4)።

**3) ኅብረትን ስለ መጠበቅ የክርስቶስ ትምህርት**

በአዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ደም የተዋጁትን ወገኖቻችንን መጠበቅ የምንችለው እርስ በርስ በመዋደድ እንደሆነ ነግሮናል።ጌታ ከሰጠን ወርቃማ ትዕዛዛት ከሁለቱ አንዱ ለሌሎች ሊኖረን ስለሚገባን ፍቅር ነው የሚናገረው። ይህ ሃሳብ በሶስቱም ወንጌላት ተጠቅሶ እናገኛለን (ማቴ 22፡39፣ማር 12፡31፣ ሉቃ 10፡29) ። እንደዚህ ይላል "…አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም" (ማር 12፡30-31)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም ኅብረት የክርስቲያኖች የህይወት መርህ እንደሆነ ያስተምራል (ሐዋ 2፡42)።

**4) ኅብረትን ስለ መጠበቅ መልዕክቶችስ ምን ይላሉ**

የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች ስለ ፍቅር እጅግ ጠቃሚ ነገሮችን ይናግራል። ፍቅርንና ኅብረትን ከሁሉም የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች ለመጥቀስ ይህ ወረቀት አይበቃንም። በህይወታችን የሚገለጡ ታዋቂ ናቸው ብለን የገመትናቸው አግልግሎቶች ቢኖሩ እንኳን የፍቅር አደራ ካልጠበቅን አይጠቅምም። የቆሮንቶስ መጽሐፍ ስለዚህ ነገር በስፋት ያስተምረናል። በ1ቆሮ 13፡1 ላይ "በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሸው ጸናጽል ሆኜአለሁ" ይላል። ኅብረትን መጠበቅ መሠረታዊ ነገር ነው። በተጠናከረ መልኩ የገላቲያ መልዕክትም እንደዚህ ይላል "ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፡- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ወደድ የሚል ነው" (ገላ 5፡14) 1ቆሮ 13፡1ዮሐ.4፡20 ።
ሐዋርያው ዮሐንስም ወንድምን መጥላት ነፍስ ከመግደል ጋር እኩል ያደርገዋል። "ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ"(1ዮሐ 3፡15)። "ማንም፡-

እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?” 1ዮሐ 4፡20)። እርስ በርስ ያለንን ኅብረት አደራ ከጠበቅን ከራሳችን አልፈን ለሌሎች በረከት እንሆናለን። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ወንድሞችና እህቶች ለኛ የተሰጡን አደራ ናቸው።

### 5) ኅብረታችንንና ፍቅራችንን እንዴት እንጠብቅ?

የተሰጡንን አደራ ወንደሞቻችን እህቶቻችንና ሌሎችንም ሰዎች መጠበቅ እንድንችል የሚረዱን ምክሮች

- በግላችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ማጠናከር (በመጸለይና ቃሉን በማንበብ)
- ጥሩ ህሊና ይኑረን
- አንደበታችንን በትክክለኛ ቦታ መጠቀም
- በይቅርታ ህይወት በየዕለቱ መኖር
- እርስ በርስ መከባበርና መጠባበቅ
- ጥበብ በተሞላ አካሄድ ሰዎችን ማቅናት
- ከአማኞች ጋር ለመተናነጽ ኅብረት ማድረግ
- በህይወታችን መንፈሳዊ ፍሬ ለማፍራት መወሰን (ገላ 5፡22)

እነዚህን መርሆችንና ምክሮችን ከተከተልን እግዚአብሔር የሠጠንን እና በረጅም ጊዜ ውስጥ ያፈራናቸውን ወገኖቻችንንና ሌሎችንም ሰዎች አንዴ በተከሰተው ችግር ምክንያት እንደቀልድ አናጣቸውም። ያጣናቸውንም ለመመለስ ኃይል ይኖረናል።

***መደምደሚያ***

እንግዲህ የኅብረትን ነገር ስናነሳ ኅብረት ከእግዚአብሔር የተሰጠ መልካም ስጦታ ብቻ ሳይሆን፣ እንድንንከባከበው ፣ እንድናሳድገው የተሰጠን አደራ ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር የሠጠንን ወንድምና እህት በስርዓቱ አለመያዝ አደራን በሚገባ አለመወጣት ነው። እግዚአብሔር ይህንን አደራ እንድንወጣ ጸጋውን ያብዛልን እኛም ለእርሱ ራሳችንን እንስጥ። በብዙ ጊዜ ሂደት ያፈራናቸውንና ጌታም በደሙ ዋጅቶ የሰጠንን ወገኖቻችንን እንጠብቃቸው እንዲሁም ያፈራናቸውን እንዳናጣ፣ ያጣናቸውን ደግሞ እንድንመልሳቸው እንትጋ።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ከወገኖች ጋር ኅብረት እንድናደርግ እንደሚፈልግ እና ኅብረት ማድረግን እንደሚወድ በምን እናውቃለን?
2. -ለምትሰጠውስ መልስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ወይንም ምሳሌ መስጠት ትችላለህ?
3. የክርስቲያኖች ኅብረት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው እንድንል የሚያደርገን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ምን አለ?
4. በዮሐ 17፡ 20-23 እንዲሁም 1ኛ ቆሮ 1:10-15 ያሉት ክፍሎች የተሰጠንን ክርስቲያናዊ ኅብረት እንድንጠብቅ የሚያሳስቡን እንዴት ነው?
5. ስለ ሁለቱ ወርቃማ ትዕዛዛት ተውያዩ። (ማቴ 22፡39፣ማር 12፡31፣ ሉቃ 10፡29) እነዚህ ኅብረትን ለመጠበቅ እንዴት ነው የሚረዱት?
6. እንደ ባለአደራ ጌታ የሰጠንን ወንድሞችና እህቶችን እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ተመካከሩ። (ገላ 5፡22)
7. እስካሁን በተመለከትነው ክፍል መሰረት፣ ስለተበላሹ ኅብረቶች ምን ትላለህ? ኅብረቱን ለማደስስ ምን ማድረግ አለብን ትላለህ?

# ጥናት ስምንት

**ባለአደራነት በቤተሰብ**

***ዓላማ፡-***

ቤተሰብ ከእግዚአብሔር የተሰጡን አደራ ስለሆኑ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንድንጠብቅ ማስገንዘብ።

***መግቢያ***

በምድር ላይ ብዙ ድርጅቶች እንዳሉ ይታወቃል። ቤተሰብ እግዚአብሔር በምድር ላይ ከሁሉም ድርጅቶች በፊት የመሰረተው ተቋም ነው። ይህም ተቋም የአዳምና የሔዋን ቤተሰብ ነው (ዘፍ 2፡18)። ከዚያ በኋላ ጌታ ብዙ ተቋማት እንዲመሠረቱ ፈቅዷል። የአዳምንና የሔዋንን ቤተሰብ አንዱን ለአንዱ አደራ ሰጥቷል። ቤተሰብን መጠበቅ ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የተሰጠ አደራ ነው። የአባት፣ የእናት፣የሚስት፣የባል ወይም የልጆች ብቻ አይደለም። ቤተሰብ የብዙ ነገሮች ጅማሬ ማዕከል እንደሆነ አስበውታል? ለምሳሌ የብዙዎች ምሁራን፣ የሃይማኖትና የሀገር መሪዎች ወዘተ መብቀያ ቦታ ነው። በአንድ በኩል የቤተሰብን አደራ በሚገባ መወጣት ጠቃሚ ዜጋዎችን እና የጌታ ሰዎችን ለማፍራት ሲረዳ (ለምሳሌ 2ኛ ጢሞ 1:5)፤ በሌላ በኩል አደራን በሚገባ አለመወጣት ደግሞ ቤታችንን ዓለምን በክፋትና በጭካኔ ለሚያናውጡ ሰዎች መብቀያ ቦታ እናደርገዋለን (ለምሳሌ ቃየል ዘፍ 4)። እግዚአብሔር በቤተሰብ ውስጥ የሰጠንን አደራ በሚገባ ለመወጣት እንድንችል፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሰጠውን ኃላፊነት ማወቅ እና መወጣት ይገባዋል። ስለዚህም በዛሬው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚሰጠውን ሃላፊነት እንመለከታለን።

**1) ባልና ሚስት**

በአዲስ ኪዳን ስለ ባልና ሚስት በብዙ ክፍሎች ተጠቅሷል። ከነዚህም ጥቂቶቹ ኤፌ 5፡21-33፣ቆላ 3፡18-21፣1ቆሮ7፡1-5 እና 1ጴጥ 3፡1-22 ናቸው። እነዚህን ክፍሎች በሚገባ ለመረዳት የሚቸግረን ሚዛኑን በጠበቀ መልክ ክፍሎቹን ስለማናነባቸው ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ ውስን ቃላቶችን፣ሐረጎችን፣ስንኞችንና አረፍተ ነገሮችን ቆራርጠን አይደለም። ሙሉውን ክፍል ወይም ሙሉውን መጽሐፍ ቀደም ያለውንና ተከታዩን አንቀጽ ሆነ አውድ በማስተያየት የማንበብና በትክክሉ የእግዚአብሔር ቃልን የመተርጎም ታላቅ አደራ አለብን። ይህንን ስናደርግ የተሳሳተ ግንዛቤንና መረዳትን እናስተካክላለን የሀሰት ትምህርትንም ቢሆን በሚገባ መቃወምና መመለስ እንችላለን። ለዛሬው ጥናት ኤፌ 5፡21-33 እና 1ጴጥ 3፡1-22 በአጭሩ እናያለን።

ኤፌ 5፡21-33 ለባልና ለሚስት ትልቅ አደራ ሰጥቷል። ሐዋርያው ጳዉሎስ ለባልና ሚስት ያለባቸውን አደራ ከመናገሩ በፊት ቀደምት የሆነን ነጥብ በቁጥር 21 ላይ “ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ” በማለት ስለ አደራቸው መሰረት ተናግሮል።

ይህን ካለ በኋላ ለሚስቶች ለባሎቻችሁ “ተገዙ” በማለት ይናገራል። ለሚስቶች ብቻ ሳይሆን ባሎችንም ሚስቶቻችሁን ውደዱአቸው፣ተንከባከቡአቸው ይላል። ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዴት እንደሚወዱ በሚያስገርም መንገድ ነው የተጠየቁት፤ እንዲህ በማለት “ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤” 5፡25-26። ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ የተጠየቁበት መስፈርት ወደር የሌለው ነው። እስከ ነፍስ መስጠት ድረስ፤ ማለትም አንዳች የምናስቀረው ነገር ሳይኖር ማለት ነው። አልገባኝም እንዳይባል ደግሞ ቀለል ያለን አገላለጽ ተጠቅሞ ባል ሚስቱን “እንደራሱ ሥጋ” ይውደድ ይላል።

ሚስት ደግሞ ልትገዛ የተጠራችበት መጠራት “. . . ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ”። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ የምትገዛው ክርስቶስ ስላሳያአት የፍቅር ምላሽ ነው።

ባልና ሚስት የሚጠበቅባቸውን ከሌላው ጋር በማወዳደር የኔ ከባድነው ወይም ይህን ሲያሟላ ስታሞላ አደርገዋለሁ ወደሚል መንፈስ መሻገር አይችሉም። እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ድርሻ የመወጣት አደራ እንጂ የሌላውን አደራ እያሳሰቡ የመኖር አደራ አልተሰጣቸውም። አደራችንን ለመወጣት መትጋትን ወይስ የሌላውን አደራ በማሳሰብ እየተጋን ነው?

በቁ. 23 "ራስ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሠራቸው ነገሮች ሁሉ በሥርዓት የተገዙ ስለሆኑ ቤተሰብም በሥርዓት እንዲገዛ መሪ መኖር ስላለበት የመምራቱን ጉዳይ ለማመልከት ብቻ ነው።መሪ አገልጋይ ነው። በ1ጴጥ 3፡1 መሰረት በጌታ የደከመውን የማጠንከርና የማበረታታት አደራ አለብን። ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ጴጥ 3፡8-22 ባልና ሚስት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ትልቅ ምክር ይሰጣል።

## 2) ***ወላጆች ለልጆች ያላቸው ኃላፊነት***

***ወላጆች ለልጆች ለሁለንተናዊ ማንነታቸው ኃላፊነት አለባቸው፡-***

ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጡ አደራ ናቸው (መዝ 127፡3)። ስለዚህ ወላጆች በተቻላቸው አቅም ሁሉ ልጆቻቸውን በማንኛውም የህይወት አቅጣጫ የመጠበቅና የመምራት ሙሉ አደራ አለባቸው። ልጆችን ስለ እግዚአብሔር ማስተማርና መመገብ ከወላጆች ይጠበቃል። ከሚከተሉት ጥቅሶች አንዳንድ ምክሮችን ልብ እንበል።

- ልጅህን አስተምረው። በዘዳ 6፡6-7 "እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥…"
- በሕይወትህ ስለ ተገለጠች የጌታ መልካም እጅ ተርክለት። በዘዳ. 6፡6-8 "አንተ ልጅህን በለው" በግብፅ የፈርዖን ባሪያዎች ነበርን እግዚአብሔርም በጽኑ እጅ ከግብፅ አወጣን…"
- የጌታን ትዕዛዝ በመጠበቅ ለሚገኝ እረፍት አስተምረው። "እርሱም እንዳዘዘን በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት እናደርጋት ዘንድ ይህችን ትእዛዝ ሁሉ ብንጠብቅ ለእኛ ጽድቅ ይሆንልናል" (ዘዳ 6፡21 እና ቁ 25)።
- ልጆቻችንን መገስጽና የቀናውን መንገድ ማሳየት ይገባል።
- ምሳ 19፡18 "ተስፋ ገና ሳለች ልጅህን ገሥጽ፥ መሞቱንም አትሻ"
  - ምሳ 22፡6 " ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም"።
- "ልጅህን ቅጣ ዕረፍትንም ይሰጥሃል ለነፍስህም ተድላን ይሰጣታል" (ምሳ 29፡17)
- ኤፌ 6፡4 "በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡቸው።" አታስመርራቸው ወይም አታስቆጣቸው። "ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥…" (ዕብ 12፡5)። ኤፌሶን መልዕክትም (ኤፌ.6፡4) ተመሳሳይ ነገር ይነግረናል።

## 3) ልጆችና ወላጆች

በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሰረት ወላጆች ለልጆች እዲያደርጉት የተሰጣቸው ሃላፊነት እንዳለ መጠን ልጆችም ለወላጆች ከእግዚአብሔር የተቀበሉት አደራ አለ። በዚህ ክፍል የልጆችን ሃላፊነት እናያለን።

### *ሀ. ወላጆችን ማክበር*

ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ "አባትህንና እናትህን አክብር" ነው (ዘጸ 20፡12)። ይህ ቃል በዘዳ 5፡16 ተደግሞ ይገኛል። ጌታችን በአዲስ ኪዳንም (በማቴ 15፡4) ነገሩን አጠናክሮ አስቀምጦታል "አባትህንና እናትህን አክብር ደግሞ። አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና" (በማቴ19፡19) "አባትህንና እናትህን አክብር ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው"። ከጌታ አፍ የወጣውን ማርቆስና ሉቃስም ተመሳሳይ ነገር ጽፈውታል (ማር 7፡10፣ 10፡19፣ ሉቃ18፡20)። በመልዕክትም እንዲህ ይላል "መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ

እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት" (ኤፌ 6፡2-3)። ይህም ድግግሞሽ የነገሩን እጅግ በጣም አስፈላጊነቱን ያጠናክራል።

### ለ. ለወላጆች መታዘዝ

ለወላጆች መታዘዝ፣ ወላጆችን ማክበራችንን የምናሳይበት አንደኛው መንገድ ነው። ለወላጁ የማይታዘዝ ወላጁን ያከብራል ማለት ቀልድ ይሆናል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ለወላጆች እንድንታዘዝ ደጋግሞ ያዛል።

•"ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና" (ኤፌ 6፡1)።

•"ልጆች ሆይ፥ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ" (ቆላ 3፡20)።

•ልጆች እንደ ሙሴና ጢሞቴዎስ ወላጆች መንፈሳዊ ነገር ስያስተምሩን እንማር። ይህ ልምድ እንኳን ባይኖር ካዛሬ በኋላ መጀመር ተገቢ ነው።

"አክብር" እና "ታዘዞ" የሚሉት ሁለት ቃላቶች ነገሩ የማወቅና የማሰላሰል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ለወላጆቻችን ኃላፍነት እንዳለብን ያሳያል። ስለዚህ እግዚአብሔር ልጆችን በተለያዩ በረከቶች ከነበኘ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ጉድለቶች ወላጆችን መርዳት ተገቢ መሆኑንም ያመለክታል።

### ሐ. ወላጆችን መርዳት

ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ሌላው ትልቅ ሃላፊነት ወላጆችን መርዳት ነው። ልጆች እያደጉ ሲሔዱ፣ ወላጆች ደግሞ እየደከሙ መሔዳቸው ግልጽ የሆነ ነገር ነው። ወላጆች አቅም በሚያጡበት ጊዜ እና ራሳቸውን መርዳት በማይችሉበት ጊዜ ወላጅን መርዳት እና መደጎም እግዚአብሔር ለልጆች የሰጠው ታላቅ አደራ ነው (1ኛ ጢሞ 5:3-8)።

## መደምደሚያ

ከላይ እንዳየነው፣ በመጀመሪያ ቤተሰብን የመሰረተው እና ለእያንዳንዱ ሃላፊነትን የሰጠው እግዚአብሔር ነው። በመጀመሪያ ባልና ሚስት እርስ በእርስ ሊወዳዱ እና ሊተሳሰቡ፣ በኋላም ደግሞ ልጆች ሲወልዱ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊያሳድጉ አደራ አለባቸው። ልጆችም ደግሞ እንዲሁ ወላጆቻቸውን በማክበር እና በመርዳት የቤተሰባቸውን አንድነት እንዲጠብቁ እግዚአብሔር ያዛል። እኛም በቤታችን ውስጥ ቦታችንን አውቀን በፍቅርና በሰላም ልንመላለስ ይገባናል።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ቤተሰብ በእግዚአብሔር የተጀመረ እና ከእግዚአብሔር የተሰጠ ኅብረት ነው የምንለው ለምንድን ነው?
2. ቤተሰብ የእያንዳንዳችን አደራ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
3. የልጆች ኃላፊነት ለወላጆች ምንድነው? "አባትህንና እናትህን አክብር" ሲል ምን ማለት ነው? ወላጆችንስ የምናከብረው እንዴት ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ ልጆቻችሁን አታስመርሯቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. በምሳ 22:6 መሰረት "ልጅህን በሚሔድበት መንገድ ምራው" ሲል ወላጅ ልጁን የሚመራው እንዴት እና ምን በማድረግ ነው?
6. ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወዳት ባል ሚስቱን እንዲሁ ይውደዳት ሲል ምን ማለቱ ነው?
7. ሚስትስ ለባልዋ ትገዛ ሲል ምን ማለቱ ነው?
8. ራሱን ችሎ የሚኖር አማኝ ወላጆቹን የሚያከብረውና የሚታዘዘው እንዴት ነው?
9. ከ2ኛ ጢሞ 3፡ 13-15 ባለው መሰረት ወላጆች ስለ ልጅ አስተዳደግ ሊማሩ የሚችሉት ነገር ምን አለ?